የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት

ደቡብ ኢትዮጵያ ነጋሪት ጋዜጣ

DEBUB ETHIOPIA NEGARIT GAZETA

OF THE SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE

፪ኛ ዓመት ቁጥር...
አርባምንጭ ታህሳስ...ቀን ፪ሺ፲፮ዓ.ም ዓ.ም

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No
Arbaminch December, 2023

አዋጅ ቁጥር ...../፪ሺ፲፮ ዓ.ም

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ሕግ ረቂቅ አዋጅ

መግቢያ

ቤተሰብ የህብረተሰብ መሰረት መሆኑን በማመን የመንግስትና የህብረተሰብ ጥበቃ ማግኘት እንዲችልየቤተሰብ ግንኙነት በህግ መደንገግና መገዛት ያለበት በመሆኑ፤

በሥራ ላይ ያለው የኢትዮጵያ የቤተሰብ ህግ ከክልላችን ተጨባጭ ሁኔታና በዋነኝነትም ከህገ-መንግስቱ ጋር እንዲጣጣም ማድረግ በማስፈለጉና በተለይም ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ መመስረት ያለበት መሆኑንና በጋብቻ አፈፃፀም በጋብቻ ዘመንና በፍቺ ጊዜ የተጋቢዎችን የእኩልነት መብት የሚያስጠብቅ እንዲሁም የልጆችን ደህንነት አስተዳደግና አጠባበቅ ቀደምትነት በሚሰጥ መልኩ ህግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በቤተሰብ ውስጥ የሚነሱ ክርክሮችን ፍትሐዊ በሆነና በተቀላጠፈ ሁኔታ ብቃት ባለው አካል እንዲዳኙ ማድረግ በማስፈለጉ፤

በክልላችን ተፈፃሚነት የሚኖረው የቤተሰብ ህግ በክልሉ መንግስት ምክር ቤት መውጣት ያለበት ስለሆነ፤

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ %4 ንዑስ አንቀጽ 3 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር----/ጀቪፒጂ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

ምዕራፍ አንድ

ስለመተጫጨት

አንቀጽ **1.** ትርጓሜ

1. መተጫጨት ማለት እጮኛውና እጮኛይቱ ለወደፊት በመካከላቸው ጋብቻ ለመፈፀም የሚያደርጉት ስምምነት ነው።
2. ስምምነታቸው በነፃ ፈቃድ ካልተመሰረተ ህጋዊ ውጤት አይኖረውም።
3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ/1/ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የተጋቢዎች ወላጆች ወይም ሌሎች ዘመዶች በመተጫጨቱ ላይ ስምምነታችን ሊሰጡ ይችላሉ።

አንቀጽ **2** የቤተዘመድ እንደራሴ

1. የቤተዘመድ እንደራሴ ሆነው የሚቆጠሩት በቅድሚያ አባትና እናት ሲሆኑ፣እነዚህ ከሌሉ ወይም ፈቃዳቸውን መስጠት የማይችሉ ከሆነ ሌሎች ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ወይም ወደ ጎን የሚቆጠሩ ዘመዶች ናቸው።
2. የቤተዘመድ እንደራሴ ከሌለ ተጋቢዎች ሌላ ሰው ሊመርጡ ይችላሉ።

አንቀጽ **3** መተጫጨትን የሚከለክል ምክንያት

በአንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ /3/ የተመለከተው ቢኖርም ጋብቻ የሚከለክል ህጋዊ ምክንያት ሳይኖር የተጋቢዎቹ ዘመዶች ለመተጫጨቱ ስምምነታቸውን አለመስጠት ምንም ለውጥ አያስከትልም።

አንቀጽ **4..**የመተጫጨት ውል አቀራረጽ/ፎርም

የመተጫጨቱ ስርዓት መተጫጨቱ በሚደረግበት ቦታ ልማድ መሰረት ወይም በጽሁፍ ይፈፀማል።

አንቀጽ **5** የመተጫጨት ማስረጃ

1 መተጫጨቱ የተደረገው በጽሁፍ በሆነ ጊዜ የመተጫጨቱ ስምምነት መኖሩን ማስረዳት

የሚቻለው ይህንኑ ጽሁፍ በማቅረብ ነው።

2 ጽሁፍ በጠፋ ጊዜ ወይም በሌላ ጊዜ በሶስት ምስክሮች ወይም ማናቸውም ማስረጃ በማቅረብ ይሆናል።

አንቀጽ **6** <u>መተጫጨት የሚቆይበት ጊዜ</u>

በመተጫጨቱ ስምምነት ውስጥ ጋብቻ የሚፈፀምበት ጊዜ ካልተወሰነ የመተጫጨቱ ስምምነት በተደረገ በአንድ ዓመት ውስጥ ጋብቻ መፈፀም አለበት።

አንቀጽ **7** <u>የመተጫጨት መፍረስ</u>

ከተጋቢዎች አንዱ ጋብቻ ለመፈፀም እንቢ ካለ ወይም በሁኔታ ወይም በጠባይ ጋብቻ እንዳይፈፀም የሚያደርግ ሁኔታ ካሳየ የመተጫጨት ስምምነት ይፈርሳል።

አንቀጽ **8** <u>የመተጫጨት መፍረስ የሚያስከትለው ውጤት</u>

1. ለመተጫጨት መፍረስ ኃላፊ የሆነው ወገን በመተጫጨቱ ምክንያት የተደረጉ ወጭዎችን ሁሉ የመክፈልና የተቀበለውን ስጦታ ለሌላው ወገን የመመለስ ግዴታ አለበት።
2. ኃላፊ የሆነው ወገን በተጨማሪ ለተጎጂው ወገን የህሊና ጉዳት ካሳ እንዲከፍል ፍ/ቤቶች ሊወስኑበት ይችላሉ።
3. ፍ/ቤት የካሳውን መጠን ለመወሰን ርትዕንና የአካባቢውን ልማድ መሰረት ያደርጋል።
4. ሆኖም የህሊና ጉዳት ካሳ መጠን ከ!ሺ /አሥር ሺ/ የኢትዮጵያ ብር የበለጠ ሊሆን አይችልም።

አንቀጽ **9** <u>የመተጫጨት መቅረት</u>

መተጫጨቱ የቀረው ከተጋቢዎቹ በአንደኛው ሞት ወይም በሁለቱም ስምምነት ከሆነ ከላይ በአንቀጽ 8 የተደነገገው ተፈፃሚ አይሆንም።

አንቀጽ **!** <u>ስለይርጋ</u>

በመተጫጨት መፍረስ ምክንያት የሚቀርቡ ክሶች ሁሉ መተጫጨቱ ከፈረሰበት ቀን አንስቶ በሁለት ዓመት ውስጥ ካልቀረቡ በይርጋ ይታገዳል።

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>

<u>ስለጋብቻ አፈፃፀም</u>

<u>ክፍል **1**</u>

ጠቅላላ

አንቀጽ !1 ልዩ ልዩ የጋብቻ ሥርዓቶች

1. ጋብቻ በአንድ የክብር መዝገብ ሹም ፊት ሊፈፀም ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ላይ የተጠቀሰው ቢኖርም፣ ጋብቻ በተጋቢዎች ኃይማኖት ወይም ባህል መሰረት ሊፈፀም ይችላል።

አንቀጽ !2 በክብር መዝገቡ ሹም ፊት የሚፈፀም ጋብቻ

ጋብቻ በክብር መዝገብ ሹም ፊት ተፈፀመ የሚባለው አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት ጋብቻ ለመፈፀም ተስማምተው በክብር መዝገቡ ሹም ፊት በመቅረብ ፈቃዳቸውን ሲገልጹና የክብር መዝገብ ሹሙም ይህንኑ ፈቃዳቸውን ሲቀበል ነው።

አንቀጽ !3 በኃይማኖት ሥርዓት መሰረት የሚፈፀም ጋብቻ

1. ጋብቻ በኃይማኖት ሥርዓት መሰረት ተፈፀመ የሚባለው አንድ ወንድና አንዲት ሴት በኃይማኖታቸው ወይም ከሁለቱም በአንዳቸው ኃይማኖት መሰረት የሚፀና ጋብቻ ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ሲፈጽሙ ነው።
2. በኃይማኖት ሥርዓት መሰረት ጋብቻ ሊፈፀም የሚችልበትና የአፈፃፀሙ ሥርዓት እንደየኃይማኖቱ ሥርዓት ይሆናል።

አንቀጽ!4 በባህል ሥርዓት መሠረት የሚፈፀም ጋብቻ

1. ጋብቻ በባህል ሥርዓት መሠረት ተፈፀመ የሚባለው አንድ ወንድና አንዲት ሴት በሚኖሩበት አካባቢ ወይም ጋብቻቸውን በሚፈፅሙበት ባህል ወይም በሁለቱ ተጋቢዎች ወይም ከሁለቱ ተጋቢዎች በአንዳቸው ባህል መሠረት የሚፀና ጋብቻ ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ሥርዓት ሲፈጽሙ ነው።
2. በባህል ሥርዓት መሠረት ጋብቻ ሊፈፀም የሚችልበትና የአፈፃፀሙ ሥርዓት እንደ አካባቢው ባህል ሥርዓት ይሆናል።

አንቀጽ !5 ከክልሉ ውጭ ስለሚፈፀም ጋብቻ

1. በተፈፀመበት አገር የጋብቻ አፈፃፀም ሕግ መሠረት ከኢትዮጵያ ውጭ የተፈፀመ ጋብቻ የህዝብን ሞራል እስካልተቃረነ ድረስ በዚህ ሕግ ተቀባይነት ይኖረዋል።
2. ጋብቻው በተፈፀመበት ክልል የጋብቻ አፈፃፀም ሕግ መሠረት ከክልሉ ውጭ የተፈፀመ ጋብቻ የሕዝብን ሞራል እስካልተቃረነ ድረስ በዚህ ሕግ ተቀባይነት ይኖረዋል።

ክፍል **2**

ሁሉንም ዓይነት ጋብቻ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

አንቀጽ !6 ፈቃድ

የሚፀና ጋብቻ ተፈፀመ የሚባለው ተጋቢዎቹ ለመጋባት ነፃና ሙሉ ፈቃዳቸውን ሲሰጡ ብቻ ነው።

አንቀጽ !7 ዕድሜ

1. ወንዱም ሆነ ሴቷ አሥራ ስምንት ዓመት ሳይሞላቸው ጋብቻ ለመፈፀም አይችሉም።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው ቢኖርም ከባድ ምክንያት ሲያጋጥም የተጋቢዎቹ ወይም ከተጋቢዎቹ የአንዳቸው ወላጆች ወይም አሳዳሪ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሰረት የፍትሕ ቢሮ ኃላፊው ከመደበኛው የጋብቻ ዕድሜ ከሁለት ዓመት ያልበለጠ ጊዜ በመቀነስ እንዲጋቡ ሊፈቅድ ይችላል።

አንቀጸ !8 የሥጋ ዝምድና

1. በቀጥታ የሥጋ ዘመዶች መካከል መፈፀም ክልክል ነው።
2. ወደ ጎን በሚቆጠር የሥጋ ዝምድና ባላቸው ዘመዳሞች መካከል ክልክላው እስከ ሰባተኛ ደረጃ ድረስ ነው።
3. የዝምድና ደረጃ አቆጣጠር የጋራ ከሆነው የግንድ ወላጅ ጀምሮ ግራና ቀኝ ያለውን ትውልድ መስመር በመቁጠር የሚገኝ ድምር ነው።

አንቀጽ !9 የ ጋብቻ ዝምድና

1. በቀጥታ የጋብቻ ዘመዳሞች መካከል ጋብቻ መፈፀም ክልክል ነው።
2. ወደ ጎን በሚቆጠር የጋብቻ ዝምድና ባላቸው ዘመዳሞች መካከል ክልክላው እስከ ሦስተኛ ደረጃ ነው።

አንቀጽ ! በሕግ ያልተረጋገጠ ልጅነት

የአንድ ሰው ተወላጅነት በሕግ መሠረት ያልተረጋገጠ ቢሆንም እንኳን በማህበረሰቡ ዘንድ በተወላጅነት የሚታወቅ ከሆነ በዚህ ሕግ በአንቀጽ !8 እና !9 መሠረት ለጋብቻ ክልክላ በቂ ነው።

አንቀጽ !1/// በጋብቻ ላይ ጋብቻ

ማንኛውም ሰው አስቀድሞ በጋብቻ የተሳሰረ ከሆነ ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ ሌላ ጋብቻ ወይም ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት መፈፀም የተከለከለ ነው።

አንቀጽ !2/1/ ጋብቻን በውክልና ለመፈጸም የማይቻል ስለመሆኑ

1. ጋብቻ ሲፈፀም ሁለቱም ተጋቢዎች ጋብቻው በሚፈጸምበት ጊዜ በግንባር ተገኝተው ፈቃዳቸውን መስጠት አለባቸው።
2. በዚህ አንቀጽንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው ቢኖርም ከባድ ምክንያት መኖሩን እና በተወካይ አማካኝነት ጋብቻውን ለመፈፀም የሚፈልገው ተጋቢ ፈቃዱን በማያሻማ ሁኔታ የገለጸ መሆኑን የፍትሕ ቢሮ ኃላፊው ሲያረጋግጥ ጋብቻው በውክልና ሊፈፀም ይችላል።

አንቀጽ **!3/2/** <u>መሠረታዊ ስህተት</u>

1. በስህተት በተገኘ ፈቃድ ምክንያት የተፈፀመ ጋብቻ አይፀናም።
2. በስህተት ምክንያት ፈቃድ ተጓደለ የሚባለው ስህተት መሠረታዊ ሆኖ ሲገኝ ነው።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ የተገለፀው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ መሠረታዊ ስህተት እንዳለ ይቆጠራል።

(ሀ) በሚያገባው ሰው ማንነት ላይ በመሳሳት ምክንያት አገባዋለሁ ብሎ ያላሰበውን ሰው ያገባ ሲሆን፣

(ለ) የሚያገባው ሰው ሊድን የማይችል ከባድ በሽታ ወይም ለተወላጆች ሊተላለፍ የሚችል ነዋሪ በሽታ ያለበት መሆኑን ሳያውቅ ያገባው ሲሆን፣

(ሐ) ከተጋቢዎቹ አንዱ ግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም የማይችል መሆኑን ባለማወቁ ምክንያት ያገባው ሲሆን፣

(መ) ከተጋቢዎቹ አንዱ ከተመሳሳይ ፆታ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የመፈጸም ልማድ ያለው በመሆኑን ባለማወቅ ምክንያት ያገባው ሲሆን።

አንቀጽ **!4** <u>በኃይል ሥራ የተገኘ ፈቃድ</u>

1. በኃይል ስራ በተገኘ ፈቃድ ምክንያት የተፈጸመ ጋብቻ አይፀናም።
2. ፈቃድ በኃይል የተገኘ ነው የሚባለው ፈቃዱን የሰጠው ተጋቢ ራሱን ወይም ከወላጆቹ ወይም ከተወላጆቹ አንዱን ወይም ሌላ ለእርሱ የቅርብ ዘመድ የሆነውን ሰው ሊፈጸምበት ከተቃረበ ከባድ አደጋ ለማዳን ሲል ፈቃዱን የሰጠ ሲሆን ነው።

አንቀጽ **!5** <u>በፍርድ የተከለከለ ሰው ጋብቻ</u>

1. በፍርድ የተከለከለ ማንኛውም ሰው ፍርድ ቤት ካልፈቀደለት በስተቀር ጋብቻ መፈፀም አይችልም።
2. ስለዚህ ጉዳይ ፍርድ ቤትን ለማስፈቀድ ለፍርድ ቤት የሚቀርበውም ጥያቄ የተከለከለው ሰው ራሱ ወይም አሳዳሪው ሊያቀርበው ይችላል።

አንቀጽ !6 በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነ ጊዜ

1. አንዲት ሴት አስቀድሞ የነበራት ጋብቻ ከቀረ በኋላ አንድ መቶ ሰማንያ ቀን ካላለፈ በስተቀር እንደገና ከሌላ ሰው ጋር ጋብቻ መፈጸም አትችልም።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስአንቀጽ /1/ የተደነገገው ቢኖርም ሴቲቱ አስቀድሞ የነበራት ጋብቻ ከቀረ በኋላ አንድ መቶ ሰማንያ ቀን ሳይሞላ፣

(ሀ) የወለደች እንደሆነ፣ ወይም

(ለ) ጋብቻ የምትፈጽመው ከቀድሞ ባሏ ጋር የሆነ እንደሆነ ወይም

(ሐ) እርጉዝ አለመሆኗ በሕክምና የተረጋገጠ እንደሆነ ወይም

(መ) በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነውን ጊዜ እንዳትጠብቅ ፍርድ ቤት የወሰነ እንደሆነ

በብቸኝት ለመኖር ስለተወሰነው ጊዜ የተደነገገው ተፈፃሚ አይሆንም።

ክፍል 3

ጋብቻ እንዳይፈፀም ስለመቃወም

አንቀጽ!7 ስለመቃወም

ጋብቻ ለመፈጸም አስፈላጊ የሆነ ሁኔታ አልተሟላም በማለት ሊፈጸም

የታሰበ ጋብቻ እንዳይፈጸም ተቃውሞ ማቅረብ ይቻላል።

አንቀጽ !8 መቃወም ስለሚችሉ ወገኖች

ጋብቻ እንዳይፈጸም መቃወም የሚችሉት ወገኖች የሚከተሉት ብቻ ናቸው፤

(ሀ) በዕድሜ ምክንያት ሲሆን፣ ወላጆች፣ዐቃቤ ሕግ ወይም ሌላ ማንኛውም

, ያገባኛል የሚል ሰው፣

(ለ) በሥጋ ወይም በጋብቻ ዝምድና ምክንያት ሲሆን የተጋቢዎቹ ወይም

የአንደኛው ተጋቢ ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች፣ 18 ዓመት የሞላቸው ወንድሞች

ወይም እህቶች ወይም ዐቃቤ ሕግ፣

(ሐ) በጋብቻ ላይ ጋብቻ ሊፈጸም ሲሆን ሌላ ጋብቻ ከሚፈጽመው ሰው ጋር

የቀደመ ጋብቻ አለኝ የሚለው ተጋቢ ወይም ዐቃቤ ሕግ።

(መ) በፍርድ መከልከል ምክንያት ሲሆን አሳዳሪው ወይም ዐቃቤ ሕግ።

አንቀጽ **!9** መቃወሚያ ስለሚቀርብበት ሥርዓትና ጊዜ

1. ጋብቻ እንዳይፈጸም የሚቀርበው መቃወሚያ በጽሁፍ ሆኖ እጅግ ቢዘገይ ጋብቻው ከሚፈጸምበት ከ!5 ቀን በፊት ለጋብቻ አስፈፃሚው ባለሥልጣን መቅረብ አለበት።
2. ጋብቻ አስፈፃሚው ባለሥልጣን በመቃወሚያው ላይ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት የተጋቢዎቹን አስተያየት መቀበል ይኖርበታል።

አንቀጽ **"** በመቃወሚያው ላይ ስለሚሰጠው ውሳኔ

1. ጋብቻ የሚያስፈጽመው ባለሥልጣን በሚቀርብለት መቃወሚያ ላይ በአምስት ቀን ውስጥ ውሣኔ መስጠት አለበት።
2. ጋብቻ አስፈፃሚው ባለሥልጣን መቃወሚያውን ባለመቀበል ጋብቻው እንዲፈጸም የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል።
3. ጋብቻ አስፈጻሚው ባለሥልጣን መቃወሚያውን የተቀበለው እንደሆነ ጋብቻው እንዳይፈጸም ማድረግ አለበት።
4. ፥በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ የተመለከተው ውሣኔ የተሰጠ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ለውሣኔው ምክንያት ያደረገውን ጉዳይ ተጋቢዎቹ ወዲያዉኑ እንዲያውቁት ማድረግ አለበት።

አንቀጽ **"1** ስለይግባኝ

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ " ንዑስ አንቀጽ / 3/ በተመለከተው ሁኔታ በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ተጋቢዎቹ ወይም ከተጋቢዎቹ አንዱ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ።
2. ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት የጋብቻ አስፈጻሚውን ባለሥልጣን ውሣኔ የሻረው እንደሆነ ባለሥልጣኑ ጋብቻውን ያስፈጽማል።

ክፍል **4**

ጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶች

አንቀጽ **"2 /1/** ሥልጣን ያለው የክብር መዝገብ ሹም

ጋብቻ ከተጋቢዎቹ አንዱ ወይም ከተጋቢዎቹ ወላጆች ወይም የቅርብ ዘመዶች አንዱ ጋብቻው ከሚፈፀምበት ጊዜ በፊት ቢ Á ንስ ለስደስት ወራት ያህል ሳያቋርጥ በሚኖርበት ቦታ በሚገኘው የክብር መዝገብ ሹም ፊት ይፈጸማል።

አንቀጽ **"3 /2/** ጋብቻ ለመፈፀም ጥያቄ ለማቅረብ እና ስለሚቀርብበት ጊዜ

ተጋቢዎቹ ጋብቻ ለመፈጸም ማሰባቸውን እጅግ ቢዘገይ ጋብቻውን ለመፈጸም ከወሰኑበት ቀን አንድ ወር በፊት ለክብር መዝገብ ሹም ማስታወቅ አለባቸው።

አንቀጽ **"4 /3/** <u>ጋብቻ የሚፈጸምበት ቀን ስለመወሰንና ስለማስታወቅ</u>

የክብር መዝገብ ሹሙ ጥያቄው እንደቀረበለት ከተጋቢዎች ጋር በመነጋገር ከወሰነ በኋላ ጋብቻው የሚፈጸምበትን ቀን በመግለጽ አመቺ በሆነው መንገድ ማስታወቂያ ያወጣል።

አንቀጽ**"5/4/** <u>የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት እና ጋብቻው መፈጸሙን ስለማስታወቅ</u>

1. ጋብቻው ሁለቱ ተጋቢዎች እና ከእያንዳንዱ ተጋቢ በኩል ሁለት ፣ሁለት ምስክሮች በተገኙበት በግልጽ ይፈጸማል።
2. ተጋቢዎቹና ምስክሮቹ ጋብቻ ለመፈጸም አስፈላጊ የሆኑትን ሁኔታዎች አለመጣሳቸውን በቃለ መሐላ ያረጋግጣሉ።
3. ተጋቢዎቹና ምስክሮቹ የመሐላ ቃል ከመስጠታቸው በፊት የሚሰጡት ቃል ስለሚያስከትለው ኃላፊነት የክብር መዝገብ ሹሙ በግልጽ ማስረዳት አለበት።
4. ሁለቱን ተጋቢዎች ጋብቻ ለመፈጸም መፍቀዳቸውን ለክብር መዝገብ ሹሙ በግልጽ ያረጋግጣሉ።
5. ሁለቱም ተጋቢዎችና ምስክሮቻቸው በክብር መዝገብ ላይ መፈረም አለባቸው።
6. ከዚህ በላይ የተገለጹት ሥርዓቶች የተፈጸሙ መሆናቸውን ሊያረጋግጥ የክብር መዝገብ ሹሙ ተጋቢዎቹ በሀጋዊ ጋብቻ የተሳሰሩ ሞናቸውን አስታውቆ ለተጋቢዎቹ የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል።

አንቀጽ **"6** <u>በኃይማኖትና በባህል ሥርዓት የሚፈፀም ጋብቻ</u>

1. በኃይማኖት ሥርዓት መሰረት ጋብቻ ሊፈፀም የሚችልበትና የአፈፃፀሙ ሥርዓት እንደየኃይማኖቱ ይወሰናል።
2. በባህል ሥርዓት መሠረት ጋብቻ ሊፈፀም የሚችልበትና የአፈፃፀሙ ሥርዓት በአካባቢው ባህል ይወሰናል።
3. በዚህ ህግ ለማንኛውም የጋብቻ አፈፃፀም መሟላት አለባቸው የተባሉት ሁኔታዎች በኃይማኖትና በባህል ሥርዓት ለሚፈጸም ጋብቻም መሟላት አለባቸው።

ክፍል **5**

<u>ስለጋብቻ ምዝገባ</u>

አንቀጽ **"7** <u>ጋብቻን ስለማስመዝገብ</u>

1. ጋብቻው የተፈጸመው በማንኛውም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት ቢሆንም አግባብ ባለው የክብር መዝገብ ሹም ወይም አግባብ ባለው አካል መመዝገብ አለበት።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ምዝገባውን ያከናወነ የክብር መዝገብ ሹም ለተጋቢዎቹ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ይሰጣል።
3. ማንኛውም ጋብቻ ከተፈጸመበት ቀን ጀምሮ ውጤት ይኖረዋል።

አንቀጽ"8 <u>የጋብቻ መዝገብ ስለማደራጀት</u>

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ "7 ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ተጋቢዎች ጋብቻቸውን ያላሰመዘገቡ ቢሆንም እንኳን የክብር ሹሙ አግባብ ባለው አካል ጋብቻ መፈጸሙን ካወቀ የጋብቻ መዝገብ በስልጣኑ ያደራጃል።
2. ይህ በሚሆንበት ጊዜ የክብር ሹሙ ተጋቢዎቹና እንደነገሩ ሁኔታ ምስክሮች ቀርበው በጋብቻ መዝገቡ ላይ እንዲፈርሙ ይደረጋል።

አንቀጽ **"9** <u>የጋብቻው መዝገብ ይዘት</u>

የጋብቻ መዝገብ የሚያመለክተው፤

(ሀ) የተጋቢዎቹን ሙሉ ስም፣የተወለዱበትን ቀንና ቦታ የመኖሪያ አድራሻቸውን፣
(ለ) የምስክሮቹን ሙሉ ስም፣የተወለዱበትን ቀንና ቦታ የመኖሪያ አድራሻቸውን፣
(ሐ) ጋብቻው የተፈጸመበትን ሥርዓት፣ ቀንና ቦታ እንዲሁም የተመዘገበበትን ቀን ይሆናል።

<u>ምዕራፍ ሦስት</u>

<u>የጋብቻ ሁኔታዎች አለመሟላት የሚያስከትለው ውጤት</u>

አንቀጽ **#** የዕድሜ ሁኔታ

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ !7 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕድሜአቸው ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች በሆኑት ሰዎች መካከል የተፈፀመ ጋብቻ በማናቸውም ሰው ወይም በዐቃቤ ሕግ ጥያቄ፣ እንዲፈርስ ይደረጋል።
2. ሕጉ የሚጠይቀው የጋብቻ ዕድሜ ከተሟላ በኋላ ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄ ማቅረብም ሆነ መወሰን አይቻልም።

አንቀጽ **#1** <u>የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና</u>

በሥጋ ወይም በጋብቻ ዝምድና ምክንያት ጋብቻ እንዳይፈጸም የተደነገገውን ክልከላ በመተላለፍ የተፈጸመ ጋብቻ በማናቸውም ባለጉዳይ ወይም በዐቃቤ ሕግ ጥያቄ እንዲፈርስ ይደረጋል።

አንቀጽ **#2** <u>በጋብቻ ላይ ጋብቻ</u>

1. በጋብቻ ላይ ጋብቻ ተፈጽሞ ከተገኘ በመጀመሪያው ወይም በሁለተኛው ተጋቢ ወይም በዐቃቤ ሕግ ጥያቄ የኋለኛው ጋብቻ እንዲፈርስ ይደረጋል።
2. ሆኖም ከተጋቢዎች አንዱ ከሞተ የጋብቻ ማፍረስ ጥያቄው ቀሪ ሆኖ ሁለቱም ጋብቻዎች ሕጋዊ ውጤት ይኖራቸዋል።

አንቀጽ **#3** <u>በፍርድ ክልከላ ምክንያት ጋብቻን ስለማፍረስ</u>

1. በፍርድ የተከለከለ ሰው ፍ/ቤት ሳይፈቅድ ጋብቻ ፈጽሞ ከተገኘ የተከለከለው ሰው ራሱ ወይም አሳዳሪው ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄውን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።
2. የተከለከለው ሰው ጋብቻው እንዲፈርስ የሚያቀርበው ጥያቄ ክልከላው ከቀረበት ቀን ጀምሮ ስደስት ወር ካለፈ በኋላ ሊቀርብ አይችልም።
3. ጋብቻው እንዲፈርስ በአሳዳሪው የሚቀርበው ጥያቄጋብቻው መፈጸሙን ካወቀበት ቀን ጀምሮ ከስድስት ወር በኋላ ወይም በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ክልከላው ከቀረ በኋላ ሊቀርብ አይችልም።

አንቀጽ **#4** <u>በኃይል ተግባር የተፈፀመውን ጋብቻ ስለማፍረስ</u>

1 ማንኛውም ሰው ተገዶ ጋብቻ ከፈጸመ፣ ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄውን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

2 ስለዚህ ጉዳይ የሚቀርበው ጥያቄ የኃይል ሥራው ከቀረበት ከስድስት ወር በኋላ እና በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ጋብቻው ከተፈፀመ ከሁለት ዓመት በኋላ ሊቀርብ አይችልም።

አንቀጽ **#5** <u>በስህተት ምክንያት የተፈጸመ ጋብቻን ስለማፍረስ</u>

1. ማንኛውም ሰው ከመሠረታዊ ስህተት በመነሳት ጋብቻ ከፈጸመ ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄውን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።
2. ስለዚህ ጉዳይ የሚቀርበው ጥያቄ መሳሳቱን ካወቀበት ቀን ጀምሮ ከስድስት በር በኋላ እና በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ጋብቻው ከተፈፀመ ከሁለት ዓመት በኋላ ሊቀርብ አይችልም።

አንቀጽ **#6** <u>በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነውን ጊዜ ስላለመጠበቅ</u>

በዚህ ሕግ በአንቀጽ!6 ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነው ጊዜአልተከበረም በሚል ምክንያት ብቻ ጋብቻ እንዲፈርስ ጥያቄ ለማቅረብ አይቻልም።

አንቀጽ **#7** <u>የጋብቻ አስፈፃሚ ባለስልጣን ሥልጣን የሌለው ስለመሆኑ</u>

ጋብቻው ያስፈጸመው ባለሥልጣን ሥልጣን አልነበረውም በማለት ብቻ ጋብቻው እንዲፈርስ ለመወሰን አይችልም።

አንቀጽ **#8** <u>የሥነ ሥርዓት አለመጠበቅ</u>

ጋብቻ አስፈፃሚው ባለስልጣን የጋብቻ አስፈፃጸም ሥርዓቶችን አልጠበቀም በማለትጋብቻ እንዲፈርስ ሊወሰን አይችልም።

<u>ምዕራፍ አራት</u>

<u>የጋብቻ ውጤት</u>

<u>ክፍል **1**</u>

<u>ጠቅላላ</u>

አንቀጽ**#9** ሁሉም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶች ተመሳሳይ ውጤት ያላቸው ስለመሆኑ፤

1. በማናቸውም ዓይነት የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት መሠረት የተፈፀመ ጋብቻ ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ ተመሳሳይ ሕጋዊ ውጤት ይኖረዋል።
2. በዚህ ረገድ ጋብቻ በክብር መዝገብ ሹም ፊት ወይም በሃይማኖት ወይም በባህል በታዘዙት ስርዓቶች መሠረት የተፈጸመም ቢሆን ልዩነት አይደረግበትም።

አንቀጽ ፱ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም

የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት በእውነት መፈጸሙ ወይም ተፈጽሟል ተብሎ መገመቱ ጋብቻውለሚያስከትለው ውጤት አስፈላጊ አይደለም።

አንቀጽ ፱ **1 /1/** የጋብቻ ውል

1. ተጋቢዎች ጋብቻቸው ንብረታቸውን በተመለከተ ስለሚያስከትለው ውጤት ጋብቻቸውን ከመፈጸማቸው በፊት ወይም እጅግ ቢዘገይ ጋብቻው በሚፈጸምበት ዕለት በውል መወሰን ይችላሉ።
2. እንዲሁም ግላዊ ግንኙነታቸውን በሚመለከት የሚኖሯቸውን መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ውል መወሰን ይችላሉ።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተጋቢዎቹ የሚያደርጓቸው ውሎች አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎችን የሚቃረኑ ሊሆኑ አይችሉም።

አንቀጽ **$2 /2/** የተጋቢዎቹ ችሎታ ማጣት

1. በፍርድ የተከለከለ ሰው የሚያደርገውን የጋብቻ ውል እርሱ ራሱ ካልፈፀመውና ፍርድ ቤት ካላጸደቀው በስተቀር ውጤት አይኖረውም።
2. በሕግ የተከለከለ ሰው የጋብቻ ውል መዋዋልን በተመለከተ ችሎታ እንዳለው ይቆጠራል።

አንቀጽ **$3 /3/** <u>የውሉ ፎርም</u>

የጋብቻ ውል በጽሁፍ ካልተደረገና አራት ምስክሮች፣ሁለት በባል ወገን ሁለት በሚስት ወገን የፈረሙበት ካልሆነ በስተቀር ውጤት አይኖረውም።

አንቀጽ **%4 ////\\\\\///4/** <u>የውሉ ሠነድ የሚቀመጥበት ቦታ</u>

1. የጋብቻ ውሉ አንድ ቅጅ በፍርድ ቤት ወይም በክብር መዝገብ ሹም ዘንድ ይቀመጣል።
2. ተጋቢዎቹ ወይም ከተጋቢዎቹ አንዱ ለማየት በፈለጉ ጊዜ እንዲሁም በፍርድ ቤት ወይም ከተጋቢዎቹ በአንዱ የተፈቀደላቸው ሰዎች የውሉን ሠነድ ለማየት ይችላሉ።

አንቀጽ **%5/5/** <u>ውል ለመዋዋል ስላለው የነፃነት ወሰን</u>

1. ተጋቢዎች በጋብቻቸው ውል ውስጥ በሌሎች ሦስተኛ ወገኖች ላይ ግዴታን የሚያስከትሉ ስምምነቶችን ማድረግ አይችሉም።
2. እንዲሁም ተጋቢዎቹ ባህልን ወይም ኃይማኖትን ወይም የአንድን አገር ሕግ በጥቅሉ በመጥቀስ ብቻ ተስማምተናል በማለት የሚያደርጉት የጋብቻ ውል ውጤት አይኖረውም።

አንቀጽ **$6/6/** <u>የጋብቻ ውል ስለማሻሻል</u>

1 የጋብቻ ውል እንዲሻሻል የቤተሰብን ጥቅም የሚጠይቅ ሲሆንና ተጋቢዎቹ ሲስማሙ ውሉን በማሻሻል ፍርድ ቤት እንዲያፀድቅላቸው መጠየቅ ይችላሉ።
2 ፍርድ ቤቱ በተጋቢዎቹ ተሻሽሎ የቀረበው የጋብቻ ውል የቤተሰቡን ጥቅም የማይጎዳ መሆኑን ሲያረጋግጥ የተሻሻለውን ውል ተቀብሎ ያፀድቃል።
3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/2/ በተመለከተው ሁኔታ ፍርድ ቤቱ ውሉን ካፀደቀው የተሻሻለው ውል በፍርድ ቤት ወይም በክብር መዝገብ ሹም ዘንድ ይቀመጣል።

አንቀጽ **$7/7/// U** <u>የሕግ ተፈፃሚነት</u>

የጋብቻ ውል በሌለ ጊዜ ወይም የጋብቻ ውል ቢኖርም በሕግ ሳይፀና የቀረ እንደሆነ ከዚህ ቀጥሎ ክፍል 2 እና 3(በዚህ ምዕራፍ) የተመለከቱት ድንጋጌዎችተፈጻሚ ይሆናል።

ክፍል 2

ጋብቻ በተጋቢዎች ግላዊ ግንኙነት ላይ ስለሚኖረው ውጤት

አንቀጽ $8 *መከባበር፣ መተጋገዝና መደጋገፍ*

1. ባልና ሚስት እርስ በራሳቸው መከባበር፣ መተጋገዝና መደጋገፍ አለባቸው።
2. በጋብቻ ውል ውስጥ ይህንን የሚቃረን ስምምነት ማድረግ አይችሉም።

አንቀጽ $9 የቤተሰብ የጋራ አመራር**/1/** ጠቅላላ

1. በቤተሰብ አመራር ረገድ ባልና ሚስት እኩል መብት አላቸው።
2. ባልና ሚስት በማናቸውም ረገድ የቤተሰቡን ደህንነት እና ጥቅም ለማስጠበቅ፣ልጆቻቸው በመልካም ሥነ-ምግባር እንዲታነፁ ተገቢ ትምህርት እንዲቀስሙና ሀላፊነት የሚሰማቸው ዜጎች ሆነው እንዲያድጉ መተባበር አለባቸው።

አንቀጽ % /2/ ከተጋቢዎቹ አንዱ ቤተሰቡን ለመምራት ስላለመቻሉ

1. ከባልና ከሚስቱ አንደኛው ችሎታ ያጣ፣የጠፋ ወይም ቤተሰቡን ጥሎ የሄደወይም ከመኖሪያ ስፍራው በመራቁም ሆነ በማናቸውም ሌላ ምክንያት ፍቃዱን ለመስጠት በማይችልበት ሁኔታ በሚገኝበት ጊዜ በአንቀጽ $9 የተመለከተውን የቤተሰብ አመራር አንደኛው ተጋቢ ብቻውን ይፈጽማል።
2. ባልና ሚስቱ በጋብቻ ውላቸው ውስጥ ይህንን የሚቃረን ስምምነት ማድረግ አይችሉም።

አንቀጽ %1 ከጋብቻ በፊት ከሌላ ስለተወለዱ ልጆች

1. ከባልና ከሚስቱ አንዱ ከጋብቻው በፊት ከሌላ ሰው የወለዷቸውን ልጆች መልካም አስተዳደግ በሚመለከት በራሱ ሀሳብና መሪነት የፈቀደውን ውሳኔ ለማድ[ግ ይችላል።
2. ይህንንን የሚቃረን ማናቸውም ስምምነት ውጤት አይኖረውም።

አንቀጽ %2 አብሮ መኖር

1. ባልና ሚስት አብረው እንዲኖሩ ይገደዳሉ።
2. ለጤናቸው አደገኛ ካልሆነ በስተቀር ባልና ሚስት ከጋብቻ የሚጠበቀውን መደበኛውን የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም አለባቸው።
3. ይህንን የሚቃረን ማናቸውም ስምምነት ውጤት አይኖረውም።

አንቀጽ **83** <u>የመኖሪያ ስፍራን ስለመወሰን</u>

ባልና ሚስት የሚኖሩበትን ስፍራ በጋራ ይወስናሉ።

አንቀጽ **%4** <u>በስምምነት ተለያይቶ ስለመኖር</u>

1 በዚህ ህግ በአንቀጽ 82 ንኡስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው ቢኖርም፣ ባልና ሚስቱ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ተለያይተው ለመኖር መስማማት ይችላሉ።

2 ስለዚህ ጉዳይ የተደነገገውን ስምምነት መለወጡ የማይገባ ካልሆነ በስተቀር ከሁለቱ ተጋቢዎች አንደኛው አስቦ ሊሰርዘው ይችላል።

አንቀጽ **%5** <u>የመተማመን ግዴታ</u>

ባል ለሚስቱ ሚስት ለባልዋ ታማኝ የመሆን ግዴታ አለባቸው።

ክፍል **3**

<u>ጋብቻ በንብረት በኩል ስለሚኖረው ውጤት</u>

አንቀጽ **%6** <u>የባልና ሚስት የግል ሀብት**/1/** ያለግብይት የተገኙ ንብረቶች</u>

ባልና ሚስቱ ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በግል የነበሯቸውን ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኃላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው ያገኟቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነውይቀራሉ።

አንቀጽ **87 /2/** <u>በግብይት የተገኙ ንብረቶች</u>

1 ባልና ሚስት ከተጋቡ በኃላ አንዱ የግል ሀብቱ በሆነ ንብረት ለውጥ ያገኘው ወይም በግል ገንዘቡ የገዛቸው ወይም የግል ንብረቱን ሽጦ የሚያገኘው ገንዘብ የግል ሀብቱ ይሆናል።

2 በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ/1/ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚሆነው በግብይት የተገኘው ንብረት የግል ይባልልኝ ብሎ አንደኛው ወገን ጥያቄ ሲያቀርብና ፍ/ቤቱ ሲያፀድቀው ብቻ ነው።

አንቀጽ **%8** <u>የግል ሀብትን ስለማስተዳደር**/1/** መሰረቱ፡-</u>

1 እያንዳንዱ ተጋቢ የግል ሀብትን ራሱ ለማስተዳደርና ገቢውንም ለመቀበል ይችላል።

2 እያንዳንዱ ተጋቢ የግል ሀብቱን ራሱ ሊያዝበት ነጻነት አለው።

አንቀጽ **89 /2/** <u>የግል ሀብት አስተዳደርን በጋብቻ ውል ስለመወሰን</u>

1 ባልና ሚስት አንደኛው የሌላውን ተጋቢ የግል ሀብት በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያስተዳድርለት እና እንደአሰፈላጊነቱ እንዲያዝበት በጋብቻ ውላቸው ሊወስኑ ይችላሉ።

2 በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ/1/ በተመለከተው አኳኃን ንብረት የማስተዳደር ስልጣን የተሰጠው ተጋቢ በሌላኛው ተጋቢ ሲጠየቅ ስለንብረቱ አስተዳደር አመታዊ የሂሳብ መግለጫ የመስጠት ግዴታ አለበት።

አንቀጽ **&/3/** <u>ስለውክልና ስልጣን</u>

ከተጋቢዎቹ አንዱ የግል ሀብቱን በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያስተዳድርለትስሌላኛው ተጋቢ ውክልና መስጠት ይችላል።

አንቀጽ **&1** <u>የባልና ሚስት የጋራ ሀብት</u>

1 ባልና ሚስት ከግል ጥረታቸውና ከግል ወይም ከጋራ ንብረታቸው የሚያገኙአቸው ገቢዎች ሁሉ የጋራ ሀብቶቻቸው ይሆናሉ።

2 በዚህ ህ ግ አንቀጽ %8 ንኡስ አንቀጽ /2/ መሰረት የአንደኛው ተጋቢ የግል ሀብት ነው ካልተባለ በስተቀር ባልና ሚስት ከተጋቡ ቢኃላ በግብይት የሚያገኙት ንብረት ሁሉ የጋራ ሀብታቸው ይሆናል።

3 በስጦታው ውል ወይም በኑዛዜው ቃል በሌላ አኳኃን ካልተመለከተ በስተቀር፣ በስጦታ ወይም በኑዛዜ ለተጋቢዎቹ የተሰጧቸው ንብረቶች ሁሉ የጋራ ሀብቶቸቸው ይሆናሉ።

አንቀጽ **&2** <u>የህግ ግምት</u>

1 አንደኛው ተጋቢ የግል ሀብቱ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር ማንኛውም ንብረት በአንደኛው ተጋቢ ስም ብቻ የተመዘገበ ቢሆንም እንኳን የጋራ ሀብት እንደሆነ ይቆጠራል።

2 የግል ንብረት መሆኑን ሶስተኛ ወገኖች የሚያውቁት ወይም ሊያውቁት የሚገባ ካልሆነ በስተቀር፣ ባልና ሚስቱ ወይም ከሁለቱ አንዱ ይኸው ንብረት የግል ነው በማለት በሶስተኛ ወገን ላይ መቃወሚያ አድርገው ሊያቀርቡበት አይችሉም።

አንቀጽ **&3** <u>ስለባልና ሚስት ገቢ **/1/** መደበኛ የገቢ አስተዳደር</u>

1 ባልና ሚስት እያንዳንዳቸው ገቢያቸውን በየራሳቸው ይቀበላሉ።

2 ባልና ሚስት በየግላቸው የሚያገኙትን ገቢ፣ የግል ወይም የጋራ የባንክ ሂሳብ በመክፈት ማስቀመጥ ይችላሉ።

3 ከባልና ከሚስት አንደኛው ሲጠይቅ፣ ሌላኛው ተጋቢ ያገኘውን የገቢ መጠን የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

አንቀጽ **&4/ /2/** <u>ልዩ ሁኔታ</u>

1. ከባልና ከሚስቱ አንዱ ገቢውን ሌላኛው ተጋቢው እንዲቀበልለት ሥልጣን ለመስጠት ይችላል።
2. ከባልና ከሚስቱ በአንደኛው ጠያቂነት የአንደኛው ገቢ ሌላኛው ተጋቢ እንዲቀበልና ለመቀበሉም ደረሰኝ እንዲሰጥ ፍ/ቤት ሊወስን ይችላል።
3. በሌላ ህግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር፣ ከባልና ከሚስት የአንደኛው ገቢ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲከበር በፍ/ቤት ሊታዘዝ ይችላል።

አንቀጽ **&5** <u>የጋራ ሀብትን ስለማስተዳደር</u>

1. ከባልና ከሚስት አንዱ የጋራ ሀብታቸውን በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያስተዳድር ግልጽ የሆነ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ባልና ሚስቱ የጋራ ሀብታቸውን በጋራ ያስተዳድራሉ።
2. ከባልና ከሚስት አንዱ ችሎታ የለውም ተብሎ ሲወሰን ወይም ንብረት የማስተዳደር መብቱንሲገፈፍ ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት የጋራ ሀብታቸውን ለማስተዳደር የማይችል ሆኖ ሲገኝ ሌላኛው ተጋቢ የጋራ ሀብቱን የማስተዳደሩን ተግባር ያከናውናል።

አንቀጽ **&6** <u>የማስታወቅ ግዴታ</u>

ከተጋቢዎች አንዱ ብቻ የጋራ ሀብታቸውን በሚያስተዳድርበት ጊዜ የሀብቱን አስተዳደር በተመለከተ ለሌላኛው ተጋቢ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት።

አንቀጽ **&7 /1/** <u>የተጋቢዎቹ ስምምነት አስፈላጊ ስለመሆኑ</u>

በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር፣ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የተጋቢዎቹ ስምምነት አስፈላጊ ነው፡

ሀ) የጋራ የሆነውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ፣ ለመለወጥ፣ ለማከራየት፣

በመያዣ ወይም በዋስትና ለመስጠት ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ

በዚሁ ንብረት ላይ ሌሎች ሰዎች መብት እንዲያገኙ ለማድረግ፣

ለ) ዋጋቸው ከብር 5) /አምስት መቶ/ ብር በላይ የሆኑ የሚንቀሳቀሱ

ንብረቶችን ወይም የገንዘብ ሠነዶችን ለመሸጥ፣ ለመለወጥ በመያዣ ወይም

በዋስትና ለመስጠት ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ለማስተላለፍ፣

ሐ) ከብር 1) /አንድ መቶ/ በላይ ዋጋ ያለውን የጋራ ንብረት ወይም ገንዘብ

ለሌላ ሰው በስጦታ ለማስተላለፍ።

መ) ከብር 5) /አምስት መቶ/ በላይ ለመበደር ወይም ለማበደር ወይም ለሌላ

ሰው ዋስ ለመሆን።

አንቀጽ **&8** <u>የስምምነት አለመኖር ስለሚያስከትለው ውጤት</u>

1. አንደኛው ተጋቢ ከዚህ በላይ የተመለከተውን ድንጋጌ ባለማክበር የውል ግዴታ ገብቶ ከተገኘ፣ ሌላኛው ተጋቢ ለፍርድ ቤት በሚያቀርበው ጥያቄ ግዴታው ሊፈርስ ይችላል።
2. ግዴታው እንዲፈርስ የሚቀርበው ጥያቄ ጠያቂው ወገን ግዴታው መገባቱን ካወቀበት ቀን ጀምሮ ከስድስት ወር በኋላ ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ግዴታው ከተገባ ከሁለት ዓመት በኋላ ሊቀርብ አይችልም።

አንቀጽ **&9** <u>የባልና የሚስት ዕዳ</u>

1. ከባል ወይም ከሚስት በግል የሚጠየቅ ዕዳ ከባለዕዳው ተጋቢ የግል ሀብት፣ የግል ሀብቱ ዕዳውን ለመሸፈን በቂ በማይሆንበት ጊዜ ከጋራ ሀብታቸው ይከፈላል።
2. ዕዳው የመጣው ለትዳራቸው ጥቅም ከሆነ ከጋራ ሀብታቸው የጋራ ሀብታቸው ዕዳውን ለመሸፈን በቂ በማይሆንበት ጊዜ ከባል ወይም ከሚስት የግል ሀብት ይከፈላል።

አንቀጽ **W** <u>ለትዳር ጥቅም እንደተደረገ የሚቆጠር ዕዳ</u>

የሚከተሉት ዕዳዎች ለትዳር ጥቅም እንደተደረጉ የሚቆጠሩ ናቸው፡

ሀ) ለባልና ለሚስት እንዲሁም ለልጆቻቸው የዕለት ኑሮ አስፈላጊ የሆኑትንነገሮች

ለማሟላት የተገቡ ዕዳዎች፣

ለ) ባል ወይም ሚስት ቀለብ ለመስጠት ያለባቸውን ግዴታ ለመወጣት የተደረጉ

ወጪዎች፣

ሐ) ከባልና ከሚስት በአንደኛው ወይም በዕዳ ጠያቂው አመልካችነት ለትዳር ጥቅም ስለመሆኑ

ፍርድ ቤት የተቀበለው ሌላ ዕዳ።

አንቀጽ **W1** <u>የትዳር ወጪዎችን ስለመሸፈን</u>

ተጋቢዎች የትዳራቸውን ወጪ ለመሸፈን እያንዳንዳቸው እንደየአቅማቸውና ችሎታቸው አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው።

አንቀጽ **W2** <u>በተጋቢዎች መካከል ስለሚደረጉ ውሎች</u>

ባልና ሚስቱ ተጋብተው በሚኖሩበት ጊዜ በመካከላቸው የሚያደርጓቸው ውሎች ፍርድ ቤት ካላፀደቃቸው በስተቀር ውጤት አይኖራቸውም።

ምዕራፍ አምስት

ስለጋብቻ መፍረስ

ክፍል **1**

ጠቅላላ

አንቀጽ **W3** **u** <u>በማናቸውም ዓይነት የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት የተቋቋሙ ጋብቻዎች እኩል ስለመሆናቸው</u>

1 ጋብቻው የተፈፀመበት ሥርዓት ማናቸውም ዓይነት ቢሆን የጋብቻው መፍረስና የሚያስከትለው ውጤት አንድ ዓይነት ነው።

2 ጋብቻው የተፈፀመው በማናቸውም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት ቢሆንም የጋብቻውን መፍረስ በተመለከተ ማናቸውም ልዩነት አይደረግም።

አንቀጽ **W4** <u>ጋብቻ ስለሚፈርስባቸው ምክንያቶች</u>

ጋብቻ የሚፈርሰው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፡

ሀ) ከተጋቢዎቹ አንዱ ሲሞት ወይም በፍርድ ቤት የመጥፋት ወይም የመሞት ውሳኔ ሲሰጥ፣ወይም

ለ) ጋብቻ ለመፈፀም መሟላት ካለባቸው ሁኔታዎች አንዱ በመጣሱ ምክንያት በሕግ መሠረት ጋብቻው እንዲፈርስ ሲወሰን፣ወይም

ሐ) የፍቺ ውሣኔ ሲሰጥ።

አንቀጽ **W5** <u>ፍቺ ስለሚወሰንበት ሁኔታ</u>

ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ ሊወሰን የሚችለው፡

ሀ) ባልና ሚስት በስምምነት ለመፋታት ሊወስኑና ይህኑ ለፍርድ ቤት አቅርበው ውሣኔያቸው ተቀባይነት ሲያገኝ ወይም

ለ) ከተጋቢዎቹ አንዱ ወይም ሀለቱ ተጋቢዎች በአንድነት ጋብቻቸው በፍቺ እንዲፈርስ

ለፍርድ ቤት ጥያቄ ሲያቀርቡ ነው።

ክፍል **2**

በስምምነት ስለመፋታት

አንቀጽ W6 <u>በስምምነትለመፋታት ስለሚቀርብ ጥያቄ</u>

1. ባልና ሚስት በስምምነት ለመፋታት የወሰኑ እንደሆነ የፍቺ ስምምነታቸውንና ፍቺው የሚያስከትለውን ውጤት በጽሁፍ ለፍርድ ቤት በማቅረብ ፍቺው እንፀዲቅላቸው መጠየቅ ይችላሉ።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው ቢኖርም ተጋብተው ስድስት ወር ያልሞላቸው ባልና ሚስት በስምምነት ለመፋታት አይፈቀድላቸውም።
3. ባልና ሚስት ለፍርድ ቤት በሚያቀርቡት የፍቺ ስምምነት ላይ ለመፋታት የወሰኑበትን ምክንያት እንዲገልጹ አይገደዱም።

አንቀጽ W7 <u>የፍርድ ቤት ሥልጣን</u>

1. በዚህ ሕግ በአንቀጽ W6 ንዑስ አንቀጽ /1/ በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት የመፋታት ጥያቄ ሲቀርብለትፍርድ ቤቱ ባልና ሚስቱን በተናጠል ወይም በአንድ ላይ በማስቀረብ ስለጥያቄያቸው ያነጋግራቸዋል፤ እንዲሁም የመፋታት ሃሣባቸውን እንዲለውጡ ይጠይቃቸዋል።
2. ባልና ሚስቱ የመፋታት ሃሣባቸውን የማይለውጡ መሆኑን የገለጹ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ ከሦስት ወር የማይበልጥ የማሰላሰያ ጊዜ በመወሰን ሊያሰናብታቸው ይችላል።

አንቀጽ W8 <u>ጉዳዩን እንደገና ስለማንቀሳቀስ</u>

1. ባልና ሚስቱ በዚህ በአንቀጽ W7 ንዑስ አንቀጽ /2/ የተመለከተው የማሰላሰያ ጊዜ ቢሰጣቸውም እንኳን በመፋታት ሃሣባቸው ከፀኑ የተሰጣቸው የማሰላሰያ ጊዜ ካበቃበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ጉዳያቸውን እንደገና በማንቀሳቀስ የፍቺ ስምምነታቸውን እንዲያፀድቅላቸው ፍርድ ቤቱን መጠየቅ ይችላሉ።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/ የተመለከተው የስድስት ወር የጊዜ ገደብ ቢኖርም ባልና ሚስቱ አዲስ የፍቺ ስምምነት ከማቅረብ የሚያግዳቸው አይኖርም።

አንቀጽ **W9** <u>የፍቺ ስምምነት ስለማጽደቅ</u>

1 ፍርድ ቤቱ የፍቺ ስምምነቱን የሚያፀድቀው የባልና ሚስቱ ትክክለኛ ፍላጎት መሆኑን እና ባልና ሚስቱ ፈቃዳቸውን በነፃ የሰጡ መሆኑን፣ እንዲሁም ስምምነቱ ከሕግና ሞራል ጋር የማይቃረን መሆኑን ሲያምን ብቻ ነው።

2 ፍርድ ቤቱ የፍቺውን ስምምነት ያፀደቀው እንደሆነ ስለፍቺው ውጤት ያደረጉትንም ስምምነት አብሮ ያፀድቃል።

3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ የተመለከተው ቢኖርም ባልና ሚስቱ ስለፍቺው ውጤት ያደረጉት ስምምነት የልጆቻቸውን ደህንነትና ጥቅም በበቂ ሁኔታ ያማያስጠብቅ ወይም የአንደኛውን ተጋቢ ጥቅም የሚገዳ ሆኖ ካገኘው ፍርድ ቤቱ የፍቺውን ስምምነት ብቻ በማጽደቅየፍቺውን ውጤት በተመለከተ ጉድለቶቹ እንዲስተካከሉ ተገቢ መስሎ የታየውን ውሣኔ ይሰጣል።

ክፍል **3**

ጥያቄ በመቅረቡ ምክንያት ስለሚወሰን ፍቺ

አንቀጽ **(** <u>የፍቺ ጥያቄ ስለማቅረብ</u>

1 ከባልና ሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱም ተጋቢዎች በአንድነት በመሆን ጋብቻቸው በፍቺ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ።

2 ከባልና ሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱም ተጋቢዎች በአንድነት በመሆን የፍቺ ጥያቄ ሲያቀርቡ ፍቺ ለመጠየቅ ምክንያት የሆናቸውን ጉዳይ መግለጽ ይችላሉ።

አንቀጽ **(1** <u>የፍርድ ቤት ሥልጣን</u>

1 በዚህ ሕግ አንቀጽ (መሠረት ጋብቻው በፍቺ እንዲፈርስ ጥያቄ ሲቀርብለት፣ፍርድ ቤቱ ባልና ሚስቱን በተናጠልም ሆነ በአንድነት በማነጋገር የፍቺው ጥያቄ የሚቀርበትንና አለመግባባቱን በስምምነት ለመፍታት የሚችሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር እንዲችሉ ያግባባቸዋል።

2 ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/ በተመለከተው መሠረት ሞክሮ ውጤትያላገኘ እንደሆነ ወይም እንደ ነገሩ ሁኔታ ውጤት የማያገኝ መስሎ የታየው እንደሆነ ባልና ሚስቱ ከፍርድ ቤት ውጭ ራሳቸው በሚመርጧቸው ሽማግሌዎች አማካኝነት ጉዳያቸውን በእርቅ እንዲጨርሱ ሊጠይቃቸው ይችላል።

3 ባልና ሚስቱ ጉዳያቸውን በሽማግሌ አማካኝነት በእርቅ ለመጨረስ ያልተስማሙ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ከሦስት ወር ያልበለጠ የማሰላሰያ ጊዜ በመወሰን ሊያሰናብታቸው ይችላል።

4 ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ተገቢውን ሁሉ አድርጎ ጥረቱ ውጤት ካላገኘ ፍርድ ቤቱ የአስታራቂ ሽማግሌዎች ሪፖርት ከደረሰው ወይም እንደሁኔታው ለተጋቢዎች የተወሰነው የማሰላሰያ ጊዜ ካበቃበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የፍቺው ውሣኔ ይሰጣል።

አንቀጽ **(2** <u>ለጊዜው የሚሰጡ ትዕዛዞች</u>

1 የፍቺ አቤቱታ ሲቀርብ ወይም በጋብቻ ውስጥ የሚፈጠር አለመግባባት በአስታራቂ ሽማግሌዎች በሚታይበት ወቅት ፍርድ ቤቱ ወዲያውኑ ባልና ሚስቱ ስለሚተዳደሩበትና ስለሚኖሩበት ሥፍራና ስለአኗኗራቸው እንዲሁም ስለንብረተቸው አስተዳደር ተገቢ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ ይሰጣል።

2 ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ በተመለከተው መሠረት ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ከሁለቱ ተጋቢዎች የአንዳቸው ከጋራ መኖሪያቸው መውጣት የግድ ሆኖ ከተገኘ የጋራ መኖሪያቸውን ለቆ ቢወጣ የባሰ ጉዳት የሚደርስበት ወገን የትኛው መሆኑን እንዲሁም የልጆችን ጥቅም ለማስጠበቅ አመቺ የሚሆነውን ሁኔታ ሁሉ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።

አንቀጽ **(3** <u>የፍቺ ውጤቶችን ስለመወሰን</u>

1 በዚህ ክፍል መሠረት ጋብቻው በፍቺ ከፈረሰ፣ ፍርድ ቤቱ ፍቺውን ስለሚያስከትለው ውጤት እንዲስማሙ ባልና ሚስቱን ይጠይቃቸዋል።

2 ባልና ሚስቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ለመስማማት ያልፈለጉ ወይም ለመስማማት ሞክረው ስምምት ላይ ለመድረስ ካልቻሉ ፍርድ ቤቱበሚሾማቸው ባለሙያዎች አማካኝነት ወይም አመቺ መስሎ በሚታው በማናቸውም ዘዴ የፍቺውን ውጤት ይወሰናል።

3 የፍቺው ውጤት በስምምነት በሚያልቅበት ወይም በሽማግሌዎች ወይም በባለሙያዎች በሚወሰንበት ጊዜ ውሣኔው ተፈፃሚነት የሚኖረው ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ነው።

4 ፍርድ ቤቱ ፍቺውን አስቀድሞ በመወሰን የፍቺውን ውጤት በተመለከተ የሚሰጠውን ውሣኔ እንደ ሁኔታው ከፍቺ በኋላ ከስድስት ወር ላልበለጠ ጊዜ ሊያዘገየው ይችላል።

አንቀጽ **(4** <u>ስለካሣ **(1)** መሠረቱ</u>

1 ከባልና ከሚስት አንዱ ለፍቺው ምክንያት የሆነውን በደል ፈጽሞ ከተገኘ ፍርድ ቤቱ ለፍትህ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በሌላው ተጋቢ ላይ ስለደረሰው ጉዳት በዳዩ ተመጣጣኝ የሆነ ካሣ እንዲከፍል ሊወሰን ይችላል።

2 ስለ ካሣ አከፋፈል አንደኛው ተጋቢ በሌላው ላይ በደል ፈጽሟል የሚባለው፡

ሀ) የመከባበር፣የመተጋገዝ፣የመደጋገፍ ግዴታን ሲጥስ፣

ለ) አብሮ የመኖር ግዴታን ያለበቂ ምክንያት ሲጥስ፣

ሐ) የታማኝነትን እና የመሳሰሉትን ሌላ የአንድ ወገን ግዴታ ጥሶ ከተገኘ ነው።

አንቀጽ **(5/** <u>የካሣው መጠን</u>

1 ፍርድ ቤቱ የካሣውን መጠን የሚወስነው የጥፋቱን ክብደት ግምት ውስጥ በማስገባት በርትዕ ነው።

2 ስለሆነም የካሣው መጠን ከብር ! ሺህ (አስር ሺህ ብር) መብለጥ የለበትም።

3 ፍርድ ቤቱ የታማንነት ግዴታ ወይም አብሮ የመኖር ግዴታ የጣሰው ተገቢ ሌላውን ተገቢ ለመጉዳት መሆኑን ሲያረጋግጥ አብላጫውን የንብረት ድርሻ ለተጎጂው ሊወሰን ይችላል።

ምዕራፍ ስድስት

የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት

አንቀጽ **(6** <u>የባልና ሚስትን ሀብት በስምምት ስለማጣራት</u>

1 በዚህ ህግ ስለካሣ ክፍያ የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ጋብቻው በዚህ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ከፈረሰ ባልና ሚስቱ የጋብቻው መፍረስ በንብረት በኩል የሚያስከትለውን ውጤት አስመልክተው በሚያደርጉት ስምምነት ወይም በጋብቻ ውላቸው መሠረት ይጣራል።

2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው የጋብቻ ውል ወይም ስምምነት የሌለ ወይም በህግ ፊት የማይፀና ሆኖ ከተገኘ የባልና ሚስት ሀብት በሚከተሉት ድንጋጌዎች መሠረት ይጣራል።

አንቀጽ **(7** <u>የግል ሀብትን መልሶ ስለመውሰድ</u>

1 ባል ወይም ሚስት የግሉ መሆኑን በማስረዳት የግል ሀብቱ የሆነውን ንብረቱን መልሶ የመውሰድ መብት ይኖረዋል።

2 ከባልና ሚስቱ አንደኛው የግል ሀብቱ የሆነ ማናቸውም ንብረት ለሌላ ሰው የተላለፈ መሆኑና ከዚሁ ግብይት የተገኘውም ገንዘብ ከጋራ ሀብታቸው ጋር የተቀላቀለ መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ፣ከዚህንብረት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ ወይም ንብረት ከጋራ ሀብታቸው በቅድሚያ የማንሳት መብት ይኖረዋል።

3 ባልና ሚስት የየግል ሀብታቸውን የሚያነሱበት ሁኔታ ሲኖር ሁለቱም በመጨረሻ ከተገኘው የንብረት መጠን እንደየአስተዋጽዎቸው ሊደርሳቸው የሚችለውን ያህል የማንሳት መብት ይኖራቸዋል።

አንቀጽ **(8** <u>ስለ ካሣ</u>

1. በዚህ ሕግ መሠረት የጋራ ንብረቱን ወይም የሌላኛውን ተጋቢ ንብረት በብቸኝነት እንዲያስተዳድር ሥልጣን የተሰጠው ተጋቢ፣ከተሰጠው ሥልጣን ውጭ በፈጸማቸው ድርጊቶች ምክንያት ወይም ከብልሹ አስተዳደር የተነሣ ወይም የካሳ ጠያቂውን መብት በማታለል ድርጊቱ የጎዳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በተበዳዩ ጥያቄ ሲቀርብለት ተገቢ የጉዳት ካሣ እንዲከፈለው ሊያዝዘይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የሚቀርብ የካሣ ጥያቄ ተፈፀመ የተባለው ድርጊት ጋብቻው ከመፍረሱ ከአምስት ዓመት በፊት የሆነ እንደሆነ ተቀባይነት አይኖረውም።

አንቀጽ **(9** <u>ያለአግባብ ስለመበልፀግ</u>

ባልና ሚስት ተቃራኒ ስምምነት ካላደረጉ በስተቀር አንደኛው ተጋቢ ሌላው ተጋቢ በግል ንብረቱ ወይም በጋራ ሀብታቸው ያለአግባብ መበልፀጉን ካስረዳ ፍርድ ቤቱ ተገቢ ካሣ እንዲከፈለው ሊያዝይችላል።

አንቀጽ **1)**<u>የ ዕዳ ጠያቂዎችን መብት ስለማስከበር</u>

ከባልና ሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱም በጋራ በፍርድ የተረጋገጠባቸው ወይም ሁለቱም ያመኑት ዕዳ መኖሩ የታወቀ እንደሆነ ይኸው ዕዳ የባልና ሚስት ሀብት ከመከፋፈሉ በፊት ተቀንሶ ይከፈላል።

አንቀጽ **1)1** የጋራ ሀብትን ስለማከፋፈል

ከዚህ በላይ የተመለከቱትና የባል ሚስት ሀብትን በስምምነት ስለማከፋፈል የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ለሁለቱም እኩል የሚከፋፈል ይሆናል።

አንቀጽ **1)2/2/**<u>የባልና ሚስት ሀብት በዓይነት የሚከፋፈል ስለመሆኑ</u>

1. በመሠረቱ እያንዳንዱ ተጋቢ ከጋራ ሀብቱ የተወሰነ ንብረት እንዲደርሰው በማድረግ የጋራ ሀብቱ በዓይነት እንዲከፋፈል ይደረጋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስአንቀጽ /1/ በተመለከተው አኳኋን እኩል ለማከፋፈል የማይቻል ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፣ልዩነቱ በገንዘብ እንዲካካስ ይደረጋል።
3. የሀብት ክፍፍሉ በሚደረግበት ጊዜ እያንዳንዱ ተጋቢ ይበልጥ ጠቃሚነት ያላቸውን ንብረቶች እንዲያገኝ ለማድረግ ጥረት መደረግ ይኖርበታል።

አንቀጽ **1)3** <u>ለማከፋፈል አዳጋች ስለሆኑ ንብረቶች</u>

1. ንብረቱ ለክፍፍል የማያመች ወይም ለማከፋፈል የማይቻል ሆኖ የተገኘ እንደሆነና ባልና ሚስቱን ንብረቱ ከሁለቱ ለአንዳቸው እንዲሰጥ ለማስማማት ሳይቻል የቀረ እንደሆነ ንብረቱ ተሸጦ የተገኘውን ገንዘብ እንዲከፋፈል ይደረጋል።

2 ስለአሻሻጡ ሁኔታ ባልና ሚስቱ ሳይስማሙ ቀርተው አንደኛው ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ ሽያጩ የሚደረገው በጨረታ ይሆናል።

አንቀጽ **1)4** ደመወዝና ጡረታ የማይከፋፈል ስለመሆኑ

1 ደመወዝና የጡረታ ክፍያ በፍቺ ጊዜ አይከፋፈልም።

2 ሆኖም ጋብቻ በሞት ምክንያት ሲፈርስ በልዩ ህግ ስለ ባልና ሚስት ድርሻ የተወሰነው የተጠበቀ ይሆናል።

አንቀጽ **1)5** <u>ጋብቻው ከፈረሰ በኋላ ከባልና ሚስት ስለሚጠበቅ ዕዳ</u>

1 ጋብቻው ከፈረሰና የባልና ሚስት ሀብት ከተከፋፈለ በኋላ የሚጠየቅ ዕዳ በጋራ መከፈል የነበረበት በሆነ ጊዜ ስለ ዕዳው አከፋፈል ሁለቱም በየድርሻቸው መጠን ተጠያቂ ይሆናሉ።

2 ዕዳው የሚመለከተው አንደኛውን ተጋቢ ከሆነ የዕዳው ክፍያ ሊጠየቅ የሚችለው ባለዕዳ ከሆነው ተጋቢ ብቻ ይሆናል።

ምዕራፍ ሰባት ጋብቻ መፈጸሙን ለማስረዳት ስለሚቀርቡ

ማስረጃዎች

አንቀጽ **1)6** <u>ጋብቻ ምስክር ወረቀት</u>

1 ጋብቻ መፈጸሙን ለማስረዳት የሚቻለው ጋብቻው በተፈጸመበት ዕለት ወይም ከዚህ በኋላ በሕጉ መሠረት ተዘጋጅቶ የተሰጠውን የጋብቻ ምስክር ወረቀት በማቅረብ ነው።

2 የክብር መዝገብ ሹም ባልተቋቋመበት ሥፍራ በመንግስት የሚወከል አካል የሚሰጠው ማስረጃ እንደ ጋብቻ ምስክር ወረቀት ይቆጠራል።

አንቀጽ **1)7** <u>የጋብቻ ምስክር ወረቀት በሌለ ጊዜ ስለሚቀርብ ማስረጃ</u>

የጋብቻ ምዝገባ ሳይደረግ የቀረ ወይም መዝገቡ በመጥፋቱ ምክንያት ጋብቻ መፈፀሙን በጋብቻ ምስክር ወረቀት ለማስረዳት ያልተቻለ እንደሆነ፣ጋብቻ ለመፈጸሙ የትዳር ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ ማስረዳት ይቻላል።

አንቀጽ **1)8** <u>የትዳር ሁኔታ መኖር **/1/**ትርጓሜ</u>

አንድ ወንድና አንዲት ሴት የትዳር ሁኔታ አላቸው የሚባሉት ራሳቸውን እንደባልና ሚስት የሚቆጥሩና ከሦስቱ በአንዱ የጋብቻ ሥርዓት መሠረት የሚኖሩ ከመሆናቸውም በላይ ቤተዘመዶቻቸውና ማኅበረሰቡ እንደባልና ሚስት የሚቀበሏቸው ሆነው ሲገኙ ነው።

አንቀጽ **1)9** <u>የትዳር ሁኔታ መኖሩን ስለማስረዳት</u>

1. የትዳር ሁኔታ መኖረን ለማስረዳት የሚቻለው አራት ምስክሮችን በማቅረብ ነው።
2. ምስክሮቹ ጋብቻ ሲፈፀም የነበሩ መሆን አለባቸው።
3. ትዳር ሁኔታ አለመኖሩንለማስረዳት የሚቻለው አራት የመከላከያ ምስክሮች በማቅረብ ነው።
4. የትዳር ሁኔታን ለማስረዳት ወይም አለመኖሩን ለማስረዳት ከምስክሮቹ በተጨማሪ ሌሎች ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል።

አንቀጽ **1)!**<u>ጋብቻ ለመፈጸሙ የትዳርሁኔታ መኖርን ስለማስረዳት</u>

1. ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ መሠረት አንድ ሰው በራሱና ከእርሱ ጋር ጋብቻ አለኝ ከሚለው ወገን ጋር የትዳር ሁኔታ መኖሩን ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ፣ ፍርድ ቤቱ ጋብቻ ተፈጽሟል ሲል የሕግ ግምት ይወስዳል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተውን ግምት ጋብቻው አለመፈፀሙን ማናቸውንም ዓይነትአስተማማኝ ማስረጃ በማቅረብ ለማፍረስ ይችላል።

<u>ምዕራፍ ስምንት</u>

ጋብቻ ሳይፈጸም እንደ ባልና ሚስት አብሮ ስለመኖር

አንቀጽ **1)!1** <u>ትርጓሜ</u>

ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ማለት አንድ ወንድና ሴት በሕግ በሚፀና አኳኋን ጋብቻ ሳይፈጽሙ በትዳር መልክ የኖሩ ሲሆን ነው።

አንቀጽ **1)!2** <u>ማብራሪያ</u>

1. ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው ኖሩ ለማለት ወንድየውና ሴትየዋ የሚያሳዩት ሁኔታ በሕግ እንደተጋቡ ሰዎች ዓይነት መሆኑ አስፈላጊና በቂ ነው።
2. ለሶስተኛ ወገኖቸ እንደተጋቡ ሆነው መቅረብ አስፈላጊ አይደለም።
3. አንድ ወንድና አንዲት ሴት በታወቀና በተደጋገመ ሁኔታ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈጸማቸው ብቻ በሁለቱ መካከል ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት ግንኙነት አላቸው ለማለት በቂ ምክንያት አይደለም።

አንቀጽ **1)!3** <u>የጋብቻ ዝምድና የሚያስከትል ስለመሆኑ</u>

1 ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር በወንድየውና በሴቲቱ የሥጋ ዘመዶች መካከል እንዲሁም በሴትየዋና በወንድው የስጋ ዘመዶች መካከል አንዳችም የጋብቻ ዝምድና አያስከትልም።

2 ሆኖም የጋብቻ ዝምድና ባለ ጊዜ ጋብቻን የሚከለክሉ ድንጋጌዎች ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ባለጊዜም ተፈፃሚ ይሆናል።

አንቀጽ **1)!4** <u>የጋብቻ ሁኔታዎች በከፊል ተፈፃሚ ስለመሆኑ</u>

ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል የተደረገው የጋብቻ ክልከላ እና የጋብቻ ዝቅተኛ ዕድሜ ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ በመኖር ጊዜ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

አንቀጽ **1)!5** <u>የጋራ ኑሮ ወጪዎችን ስለመሸፈን</u>

ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ሰዎች የጋራ ኑሮአቸውን ወጪ ለመሸፈን እያንዳንዳቸው እንደየአቅማቸውና ችሎታቸው አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው።

አንቀጽ **1)!6** <u>ስለጋራ ሀብት</u>

1 የንብረት አስተዳደራቸውን አስመልክቶ የሚያደርጉት ውል እንደተጠበቀ ሆኖ ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደ ባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ሰዎችከሦስት ዓመት ላላነሰ ጊዜ አብረው ከኖሩ በግንኙነቱ ውስጥ እያሉ ያፈሩዋቸው ንብረቶች የጋራ ሀብታቸው ይሆናል።

2 ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ አብረው በመኖር ላይ እያሉ የሚኖራቸው ንብረቶች በግንኙነቱ ውስጥ የተፈሩ ሀብቶች ተደርገው ይቆጠራሉ።

3 ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ወንድና ሴት የሚገዟቸው ዕዳዎች አብረው በሚኖሩበት ጊዜ ለጋራ ኑሮአቸው ወይም ከግንኙነቱ የተወለዱ ልጆችን መሠረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት ሲባል የተገቡ ዕዳዎች ሲሆኑ፣ ለዕዳዎቹ አከፋፈል ሁለቱም በአንድነትና በነጠላ ኃላፊዎች ይሆናሉ።

አንቀጽ **1)!7** <u>የጋራ ንብረት ስለሚያስከትለው ውጤት</u>

በዚህ ሕግ በአንቀጽ 1)!6 ንዑስ አንቀጽ /1/ በተመለከተው መሠረት የጋራ ሀብት በሚፈጠርበት ጊዜ ስለንብረቱ አስተዳደር፣የሶስተኛ ወገን ዕዳ አከፋፈልና ንብረት ማጣራት ሂደት በዚህ ሕግ በጋብቻ ስለሚፈጠር የጋራ ንብረትና የማጣራት ሂደት የተነገሩት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።/አንቀጽ (6-1)5/

አንቀጽ **1)!8** <u>የልጆች መወለድ</u>

ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብረው ከሚኖሩ ወንድና ሴት የተወለዱ ልጆች ተወላጅነታቸው የሚያረጋግጥው በዚህ ሕግ ስለመወለድ በተመለከተው ምዕራፍ ውስጥ በተደነገገው መሠረት ይሆናል።

አንቀጽ **1)!9** <u>የግንኙነት መቋረጥ</u>

1 ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ወንድና ሴት በማንኛውም ጊዜ ግንኙነታቸው እንዲቋረጥ ማድረግ ይችላሉ።

2 በዚህ ሕግ በአንቀጽ 1)!6 ስለጋራ ሀብት የተነገረው እንደተጠበቀ ሆኖ ግንኙነቱ እንዲቋረጥ ያደረገው ወገን ጥፋት ካልፈጸመ በስተቀር ካሣ እንዲከፍል አይገደድም።

አንቀጽ **1)!** <u>የግንኙነት ማስረጃ</u>

1 ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን የግንኙነት ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ በቂ ምስክሮች በማቅረብ ማስረዳት ይቻላል።

2 አንድ ወንድና አንዲት ሴት ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደ ባልና ሚስት አብረው ይኖራሉ የሚባለውምንም እንኳ በህግ የተጋቡ ባይሆንም የተጋቡ ሰዎችን ሁኔታ ሲያሳዩና ቤተዘመዶቻቸውና ጎረቤቶቻቸው እንደተጋቡ ሰዎች የሚኖሩ ናቸው ብለው ሲገምቷቸው ነው።

3 ከዚህ በላይ የተመለከተውን የሕግግምት ለማፍረስ በቂ ምስክሮች በማቅረብ የግንኙነቱን አለመኖር ማስረዳት ይቻላል።

4 የግንኙነቱን መኖር ወይም አለመኖር ለማስረዳት ከምስክሮች በተጨማሪ ሌሎች ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል።

አንቀጽ **1)!1** <u>ጋብቻ ሳይፈጸም የሚደረጉ ሌሎች ግንኙነቶች</u>

1 ከጋብቻ ሥርዓት ወይም ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ ከመኖር ውጭ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል የሚደረጉ ሌሎች ግንኙነቶች በሕግ ፊት ምንም ውጤት አይኖራቸውም።

2 በዚህ ሕግ ስለጉዲፈቻ ልጅ ወይም ልጅነትን ስለመቀበል ወይም በፍርድ አባትነህ ስለማለት የተወሰኑት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከእንደዚህ ያለ ግንኙነት የተወለዱ ልጆች ከእናታቸው በስተቀር ከሌላ ሰው ጋር ማናቸውም ዓይነት ሕጋዊ ግንኙነት አይኖራቸውም።

<u>ምዕራፍ ዘጠኝ</u>

በጋብቻ እና ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ በመኖርየሚነሱ ክርክሮችን ስለመወሰን

ክፍል 1

ጠቅላላ

አንቀጽ 1)!2 <u>ተፈጻሚነትስለሚኖረው ሕግ</u>

በዚህ ሕግ የተመለከቱት የሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ህግ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ለሚነሱ ክርክሮች የኢትዮጵያ የፍትሐብሄር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

አንቀጽ 1)!3 <u>የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት የተደነገጉት ተፈጻሚ ስለመሆናቸው</u>

1 ጋብቻው የፈረሰው በፍቺ ባይሆንም የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት ከዚህ በላይ በምዕራፍ ስድስት የተደነገጉት እንደየአግባብነታቸው ተፈፃሚ ይሆናሉ።

2 በተለይም ጋብቻው የፈረሰው በሞት በሆነ ጊዜ በሕይወት ባለው ተጋቢ እና በሟች ወራሾች መካከል የንብረት ክፍፍልን በተመለከተ ክርክር የተነሣ እንደሆነ፣ የባልና የሚስት ሀብት ስለማጣራት በዚህ ሕግ በምዕራፍ 6 የተደነገጉት እንደየአግባብነታቸው ተፈፃሚ ይሆናሉ።

አንቀጽ 1)!4 <u>የጋብቻ ሁኔታዎች ባለመሟላታቸው ምክንያት የጋብቻ መፍረስ ውጤት</u>

1 የጋብቻ ሁኔታዎች ከመጓደሉ የተነሣ/ቤት ጋብቻ እንዲፈርስ በሚወሰንበት ጊዜ መፍረሱ የሚያስከትለውን ውጤት በርትዕ ይወሰናሉ።

2 በተለይም ዳኞች ተጋቢዎቹ ጋብቻውን የፈፀሙት በቅን ልቦና ወይም በመጥፎ ልቦና መሆን አለመሆኑን፣ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ወይም አለመፈፀሙን፣ ከጋብቻ የተወለዱትን ልጆችና በቅን ልቦና ከሦስተኛ ወገኖች ጋር የተደረገውን ጥቅም ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው።

አንቀጽ 1)!5 <u>የባልና ሚስት ክርክር ስለሚይታበት ሁኔታ</u>

ፍርድ ቤት የባልና ሚስትን ክርክር በሚያይበት ጊዜ እንደነገሩ ሁኔታ አስፈላጊ ሆኖካገኘው፣ባልና ሚስቱን በአንድነት ወይም በተናጠል ሲያነጋግር ወይም ጉዳዩን ሲመረምር ምስክር ሲሰማ በዝግ ያስችላል።

አንቀጽ 1)!6 <u>ስለውሳኔ አሰጣጥ</u>

ፍርድ ቤቱ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ፍቺ በሚወሰንበት ጊዜ የተጋቢዎቹን ወይም የቤተዘመዶቻቸውን መልካም ስም ለመጠበቅ ዝርዝር ጉዳዮችን ከመተቸት በመቆጠብ ፍቺውን ለመወሰን የሚያስችሉ ምክንያቶች መኖራቸውን ብቻ በውሳኔ ላይ ሊያሰፍር ይችላል።.

አንቀጽ **1)!7** <u>ስለ ይግባኝ</u>

ፍርድ ቤቱ ፍቺ መወሰኑን ብቻ መሠረት በማድረግ ይግባኝ መጠየቅ አይችልም።

አንቀጽ **1)!%** <u>የልጆችን አጠባበቅና አያያዝ በሚመለከት ፍርድ ቤቱ ስለሚሰጠው ውሣኔ</u>

1 ፍርድ ቤቱ ጋብቻው አንዲፈርስ ሲወስን ልጆቹ ከማን ጋር ሊኖሩ እንደሚገባ፣ስለትምህርታቸው እና ስለጤናቸው አጠባበቅ፣ ስለቀለባቸውና በአጠቃላይም ስለ አኗኗራቸው፣ እንዲሁም ወላጆችና ልጆቻቸው ለመጠያየቅ ስላላቸው መብት መወሰን አለበት።

2 ፍርድ ቤቱ ከዚህ በላይ በተመለከተው ሁኔታ ውሣኔ በሚሰጥበት ጊዜ የወላጆቹን የገቢ፣ ዕድሜ፣የጤና እና የአኗኗር ሁኔታ እንዲሁም የልጆችን የዕድሜ፣ ጥቅማቸውና ፍላጎታቸው የሚጠበቅበትን ሁኔታ ማገናዘብ ይኖርበታል።

3 ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ መሠረት ስለልጆች አያያዝና አጠባበቅ የሚሰጠው ውሣኔ የሁኔታዎች መለወጥን ምክንያት በማድረግ በሚቀርብ ጥያቄ ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ ይችላል።

አንቀጽ **1)!9** <u>ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት አብሮ ስለመኖር</u>

በዚህ ክፍል የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደየአግባብነታቸው ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብረው በሚኖሩ ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

<u>ክፍል **2**</u>

<u>ስለፍርድ ቤት ሥልጣን</u>

አንቀጽ **1)"** <u>የሚፀና ጋብቻ ስለመኖሩ</u>

ጋብቻ የተፈፀመ ወይም የሚፀና ስለመሆኑ ክርክር የተነሣ እንደሆነ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የሚኖረውፍርድ ቤት ብቻ ነው።

አንቀጽ **1)"1** <u>ጋብቻ ሳይፈጸም እንደ ባልና ሚስት አብሮ ስለመኖር</u>

በአንድ ወንድና ሴት መካከል ጋብቻ ሳይፈጸም እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ስለመኖሩ ክርክር የተነሳ እንደሆነ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የሚኖረው ፍርድ ቤት ብቻ ነው።

አንቀጽ **1)"2** <u>ስለፍቺና ስለፍቺ ውጤቶች</u>

ፍቺን የመወሰን ወይም በዚህ ሕግ አንቀጽ (3 በተደነገገው መሠረት የፍቺ ውጤቶችን በተመለከተ ውሣኔ የመስጠት ወይም የማጽደቅ ሥልጣን የፍርድ ቤት ብቻ ነው።

አንቀጽ **1)"3** <u>በጋብቻ ውስጥ ስለሚፈጠሩ አለመግባባቶች</u>

1 በዚህ ሕግ በአንቀጽ 1)"2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በጋብቻ ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች ባልና ሚስቱ በሚመርጧቸው ሽማግሌዎች አማካኝነት ይወሰናሉ።

2 ሽማግሌዎች በሚሰጡት ውሣኔ ቅር የተሰኘ ወገን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታ ለማቅረብ ይችላል።

3 ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ቅሬታ ምርምሮ በሽማግሌዎች የተሰጠውን ውሣኔ ሊያፀና፣ ሊያሻሽል ወይም ሊሽር ይችላል፤ የሚሰጠውም ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል።

<u>ክፍል **3**</u>

<u>ስለ እርቅ</u>

አንቀጽ **1)"4** <u>አስታራቂ ሽማግሌዎችን ስለመምረጥ</u>

1 በዚህ ሕግ አንቀጽ (1 ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት ባልና ሚስት ጉዳያቸውን በእርቅ ለመጨረስ ከወሰኑ፣አመቺ ሆኖ በሚያገኙት መንገድ አንድ ወይም ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ሽማግሌዎችን በመምረጥ ሽማግሌ እንዲመርጡ ከተነገራቸው ቀን አንስቶ በ!5 ቀናት ውስጥ የሽማግሌዎቹን ስም ዝርዝር ለፍርድ ቤቱ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።

2 ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የሽማግሌዎች ስም ዝርዝር ሲቀርብለት ወይም ሽማግሌዎቹ እንደቀረቡ ወዲያውኑ መዝግቦ እርቅ የሚከናወንበትን የመፍትሔ አቅጣጫ የሚጠቁም ምክርና መመሪያ በመስጠት ወይም እንዲደርሳቸው በማድረግ የእርቁ ወይም የእርቁ ሙከራ ውጤት በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ እንዲቀርብለት ያዛል።

3 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ ድንጋጌ ቢኖርም ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የእርቁ ሂደት የደረሰበትን ደረጃ በየጊዜው ለመመርመርና ወቅታዊ ሪፖርት እንዲቀርብለት ማዘዝ ይችላል።

አንቀጽ **1)"5** <u>ስለተጨማሪ ጊዜ</u>

ከእርቅ ሙከራው ሂደት አኳያ ባልና ሚስት ያለመግባባታቸውን በእርቅ ሊጨርሱ ይችላሉ የሚል ግምት ያለው እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በዚህ ሕግ በአንቀጽ 1)"4 በተመለከተው ጊዜ ሳይገደብ ከአንድ ወር ያልበለጠ ተጨማሪ ጊዜ በመስጠት የእርቅ ሙከራው እንዲቀጥል ሊያዝ ይችላል።

አንቀጽ **1)"6** <u>የአስታራቂ ሽማግሌዎች ኃላፊነት</u>

1 አስታራቂ ሽማግሌዎች ባልና ሚስቱ የመፋታት ሃሳባቸውን እንዲተውና ጉዳያቸውን በመግባባበት እንዲጨርሱ ለማድረግ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ አለባቸው።

2 አስታራቂ ሽማግሌዎቹ ጉዳዩ ከፍቺ በመለስ ሊፈታ እንደማይችል የተረዱ እንደሆነ ተጨማሪ ጊዜ ሳያስፈልጋቸው ስለደረሱበት ውጤት ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው።

3 አስታራቂ ሽማግሌዎች ጉዳዩን ከፍቺ በመለስ በማግባባት ለመፍታት ከመጣር አልፈው ባልና ሚስቱን የሚመለከት ማናቸውንም ትዕዛዝ ሆነ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን አይኖራቸውም።

አንቀጽ **1)"7** <u>ሪፖርት አለመቅረብ</u>

1 በዚህ ሕግ በአንቀጽ 1)"4 እና 1)"6 መሠረት አስታራቂዎቹ ሪፖርት ሳያቀርቡ የቀሩ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ይዘጋዋል።

2 መዝገቡ በተዘጋ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ባልና ሚስቱ ወይም ከሁለቱ አንዳቸው ጉዳቸውን በእርቅ አለመጨረሳቸውንና ሪፖርቱ በወቅቱ ያልቀረበበትን ምክንያት በመግለጽ ጉዳያቸው እንዲንቀሳቀስላቸው የጠየቁ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጥያቄያቸው ተገቢ ሆኖ ካገኘው መዝገቡን በመክፈት በህጉ መሠረት የራሱን ውሣኔ ይሰጣል።

3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የሚሰጠው መዝገቡን የመዝጋት ውሣኔ ባልና ሚስቱ ወይም ከሁለቱ አንዳቸው አዲስ አቤቱታ በማቅረብ ጉዳያቸው እንዲታይላቸው ከመጠየቅ የሚያግዳቸው አይሆንም።

<u>ምዕራፍ አሥር</u>

<u>ስለመወለድ</u>

<u>ክፍል **1**</u>

አባትነትና እናትነት ስለማወቅ

ንዑስ ክፍል 1

አጠቃላይ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 1)"%የሕጉ ድንጋጌዎች አስገዳጅ ስለመሆናቸው

ሕጉ በግልጽ የሚፈቅድ ካልሆነ በስተቀር አባትነትና እናትነት ለማወቅ የተደነገጉት በዚህ ሕግ ድንጋጌዎች በስምምነት ሊለወጡ አይችሉም።

አንቀጽ 1)"9 ስለእናትነት

እናት የተባለችው ሴት ልጁን የወለደችው በመሆንዋ ብቻ እናትነቷ ይታወቃል።

አንቀጽ 1)#ስለአባትነት

1. ልጁ በሚፀነስበት ወይም በሚወለድበት ጊዜ በእናትየዋና በአንድ ወንድ መካከል በሕግ የታወቀ ግንኙነት ለመኖሩበመረጋገጡ ምክንያት አባትነት ሊታወቅ ይችላል።
2. አባትየው ልጁን ልጄ ነው ሲል በዚህ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት በመቀበሉ ምክንይትም አባትነት ሊታወቅ ይችላል።
3. በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሣኔም አባትነት እንዲታወቅ ሊደረግ ይችላል።

ንዑስ ክፍል 2

አባትነት በሕግ ግምት የሚታወቅ ስለመሆኑ

አንቀጽ 1)#1vv ባል አባት ነው ተብሎ የሚገመት ስለመሆኑ

በጋብቻ ውስጥ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባቱ ነው የሚባለው ባልየው ነው።

አንቀጽ 1)#2 c¾ የግምቱ አጠቃላይነት

1. ከልጁ ጋር ያለው እናት ግንኙነት በየትኛውም ዘዴ የተረጋገጠ ቢሆንም ከዚህ በላይ በአንቀጽ 1)#1 የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።
2. የልጁ የልደት ምስክር ወረቀት ባልየው አባት ያለመሆኑን ወይም የልጁ አባት ሌላ ሰው መሆኑን የሚያመለክት ቢሆንም እንኳ ይኸው ድንጋጌ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።
3. ከዚህ በላይ የተመለከተው ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ የልደት ምስክር ወረቀቱ እንዲታረም ይደረጋል።

አንቀጽ **1)#3** <u>እርግዝናው ስለሚቆይበት ጊዜ</u>

1 ጋብቻው ከተፈፀመ ከ 1)W ቀናት በኋላ ወይም ጋብቻው በፈረሰ በ 3) ቀናት ውስጥ የተወለደ እንደሆነ ልጁ በጋብቻው ውስጥ እንደተፀነሰ ይቆጠራል።

2 ይህን የህግ ግምት በተቃራኒ ማስረጃ ማስተባበል አይቻልም።

አንቀጽ **1)#4** <u>የባልየው መጥፋት/አለመኖር/</u>

በዚህ ሕግ ስለ አባትነት የተደነገጉት የሕግ ግምቶች በሕግ አባት ነው የሚባለው ሰው መጥፋቱ በተነገረበት ፍርድ ላይ ስለ መኖሩ የተሰማበት የመጨረሻ ቀን ነው ከተባለበት ከ 3) ቀናት በኋላ ለተወለደው ልጅ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

አንቀጽ **1)#5** <u>ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር</u>

1 ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብረው በሚኖሩበት ጊዜ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባት በዚህ ግንኙነት ከእናትየው ጋር አብሮ የሚኖር ሰው ነው።

2 በዚህ ሕግ አንቀጽ 1)#2 እና 1)#3 e ስለግምቱ አጠቃላይነት እና እርግዝናው ስለሚቆይበት ጊዜ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በዚህ አንቀጽ የተመለከተው የህግ ግምት ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

ንዑስ ክፍል **3**

<u>ልጅነትን ስለመቀበል</u>

አንቀጽ **1)#6** <u>መሠረቱ</u>

ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የልጁ አባት ማን እንደሆነ ሊታወቅ ያልቻለ ሲሆን አባትየው ልጄ ነው ሲል በመቀበሉ አባትነት ሊታወቅ ይችላል።

አንቀጽ **1)#7** <u>ትርጓሜ</u>

አንድ ሰው አንድን የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ የእርሱ ልጅ መሆኑን አምኖ በመቀበል ቃሉን የሰጠ እንደሆነ የልጁ አባት መሆኑን ተቀበለ ይባላል።

አንቀጽ **1)#%** <u>ሥርዓት/ፎርም/</u>

አንድ ሰው የክብር መዝገብ ሹም ፊት በመቅረብ አባት መሆኑ በግልጽ በሚሰጠው ቃል ወይም በጽሁፍ በሚያደርገው ኑዛዜ ወይም በሌላ በማናቸውም ስልጣን በተሰጠው ባለሥልጣን በተረጋገጠ ሰነድ አማካኝነት አባት መሆኑን በመግለጽ ልጅነትን ለመቀበል ይችላል።

አንቀጽ **1)#9** <u>ስለወኪልነት</u>

1. አካለ መጠን ያልደረሰ ቢሆንም እንኳን ልጇ ሲል ቃል ለመስጠት የሚችለው አባት ብቻ ነው።
2. ቃሉን ሌላ ሰው እንዲሰጥለት ማድረግ የሚችለው በፍርድ ቤት የፀደቀ ልዩ ውክልና ስልጣን በመስጠት ብቻ ይሆናል።
3. በፍርድ የተከለከለ ሰው ቃሉን በራሱ ወይም ፍርድ ቤት ሲፈቅድ በእርሱ ስም በህጋዊ ወኪሉ አማካኝነት ሊሰጥ ይችላል።

አንቀጽ **1)$** <u>የአባትየው መሞት</u>

የልጅ አባት የሞተ ወይም ፈቃዱን ለመስጠት የማይችል በሆነ ጊዜ ከአባትየው ወላጆች አንድ በእርሱ ስም ልጅን ሊቀበል ይችላል።

አንቀጽ **1)$1** <u>እናት ተቀባዩን አባትነት ስለማመኗ</u>

1. የልጁ እናት የተቀባዩን አባትነት እውነትነት ያለው መሆኑን ካላመነች በስተቀር አባት ልጇ ነው ሲል የሚሰጠው ቃል በሕግ ፊት ውጤት አይኖረውም።
2. የልጁ እናት የሞተች ወይም ፈቃዷን ለመግለጽ የማትችል ሆና የተገኘች እንደሆነ፣የእምነት ቃሉ ከልጁ እናት ወላጆች በአንደኛው ሊሰጥ ይችላል።
3. የልጁ እናት ወላጆች በሌሉ ጊዜ ወደ ላይ በሚቆጠር ሌላ ወላጅ ወይም በፍርድ በተከለከለው ሰው አሳዳሪ ሊሰጥ ይችላል።

አንቀጽ **1)$2** <u>ስለልጁ ለአካለ መጠን መድረስ</u>

ልጅነት የመቀበሉ ተግባር የተከናወነው ልጁ አካለ መጠን ከደረሰ በኋላ የሆነ እንደሆነ አባት ልጁን መቀበሉ ውጤት የሚያገኘው ልጁ አባትነቱን የተቀበለ እንደሆነ ነው።

አንቀጽ **1)$3** <u>አምኖ የመቀበሉ ሁኔታ</u>

በዚህ ሕግ በአንቀጽ 1)$1 እና 1)$2 የተመለከቱት ሰዎች የመቀበሉ ድርጊት መከናወኑን ካወቁበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ክርክር ያላነሱ እንደሆነ አምኖ እንደተቀበሉ ይቆጠራል።

አንቀጽ **1)$4** <u>የልጁ መሞት</u>

ልጅየው ወደ ታች የሚቆጠሩ ተወላጆችን ተክቶ ካልሞተ በስተቀር ልጅነቱን አውቆ መቀበል አይችልም።

አንቀጽ **1)$5** <u>ቃልን ስለመሻር</u>

1 ልጁ ነው ሲል አባት የሰጠውን ቃል መሻር አይችልም።
2 አሳዳሪው አስቀድሞ ስምምነቱን ካልሰጠ በስተቀር ልጅነትን የተቀበለ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ አካለ መጠን እስካልደረሰበት ጊዜ ድረስ እና አካለ መጠን ከደረሰ በኋላ እስከ አንድ አመት ጊዜ ድረስ ልጁ ነው የሰጠውን ቃል ሊሽር አይችልም።
3 ልጁ ነው ሲል የተቀበለበትን ቃሉን ለመሻር ብቸኛ መብት ያለው አካለ መጠን ያልደረሰው ብቻ ነው።የልጁ ሕጋዊ ወኪሎችም ሆኑ ወራሾች በዚህ መብት መጠቀም አይችሉም።

አንቀጽ **1)$6** <u>ለማፍረስ</u>

1 ልጅነትን ለመቀበል የተነገው ቃል በኃይል የተሰጠ መሆኑን በማስረዳት ሊፈርስ ይችላል።
2 ልጁ ነው ብሎ ከተቀበለው ሰው ሊፀነስ የማይቻል ለመሆኑ የማያሻማ አኳኋን ካልተረጋጠ በስተቀር ልጅነት የመቀበሉ ድርጊት በስህተት ወይም በማታለል የተደረገነው በማለት ሊፈርስ አይችልም።

አንቀጽ **1)$7** <u>አንድን ልጅ ብዙ አባቶች ሊቀበሉት ስላለመቻላቸው</u>

ቀደም ሲል የተሰጠ ልጅነትን የመቀበል ቃል እንዲፈርስ ካልተደረገ በስተቀር ሌላ ሰው ልጁ ነው ሲል የሚሰጠው ቃል ተቀባነት አይኖረውም።

<u>ንዑስ ክፍል **4**</u>

<u>በፍርድ ቤት ውሣኔ አባትነት እንዲታወቅ ስለማድረግ</u>

አንቀጽ **1)$%/** <u>በፍርድ ስለሚነገር አባትነት</u>

ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የልጁ አባት ያልታወቀ ወይም የተካደ እንደሆነና ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲሟሉ አባትነት በፍርድ ቤት ውሣኔ ሊታወቅ ይችላል።

ሀ)ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ በእናቲቱ ላይ የመደፈር ወይም የመጠለፍ ተግባር የተፈጸመባት ሲሆን፣

ለ) ሆነ ተብሎ በተደረገ የተንኮል ድርጊት ሥልጣንን ያለ አግባብ በመጠቀም አገባሻለሁ ሲል የተስፋ ቃል በመስጠት ወይም በሌላ ተመሳሳይ መንገድ ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ በእናቲቱ ላይ የማሳት ተግባር የተፈጸመባት ሲሆን፣

ሐ) አባት ነው በተባለው ሰው የተጻፈና በማያሻማ ሁኔታ አባትነቱን የሚያረጋግጡ ደብዳቤዎች ወይም ሌሎች ጽሑፎች ሲኖሩ፣

መ) በሕግ የታወቁ ግንኙነት ሳይኖራቸው የልጁ እናትና አባት የተባለው ሰው በሕግ በተመለከተው የእርግዝና ጊዜ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በግብረ ሥጋ ግንኙነት አብረው የኖሩ እንደሆነ፣

ሠ) አባት ነው የተባለው ሰው ልጁን በመንከባከብ በማስተማር ወይም በማሳደጉ ላይ እንደ አባት በመሆን የተሳተፈ እንደሆነ።

አንቀጽ **1)$9/ /**<u>አባትነትን በፍርድ ለማረጋገጥ ስለሚቀርብ ክስ</u>

ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን አባትነት በፍርድ እንዲነገር የሚቀርብ ክስ ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ባሉ ጊዜ ተቀባይነት አይኖረውም።

ሀ) ሌላኛው ሰው የልጁ አባት ላለመሆኑ በደም ምርመራ ወይም በሌላ አስተማማኝ የሕክምና ዘዴ ካልተረጋገጠበስተቀር በሕግ በተወሰነው የእርግዝና ጊዜ ውስጥ እናቲቱ ከሌላ ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀምዋ የተረጋገጠ እንደሆነ፣

ለ) አባት ነው የተባለው ሰው በህግ በተወሰነው እርግዝና ጊዜ ውስጥ በመጥፋቱ ወይም በአደጋ ምክንያት አባት ሊሆን የማይችልበት ሁኔታ ሲረጋገጥ፣

ሐ) አባት ነው የተባለው ሰው በደም ምርመራ ወይም በሌላ አስተማማኝ የሕክምና ዘዴ የልጁ አባት ሊሆን የማይችል መሆኑን ሲያረጋገጥ።

አንቀጽ **1)%** <u>ሌላ ሁኔታ ስለመኖሩ</u>

በዚህ ህግ አንቀጽ 1)$% በተመለከቱት ሁኔታዎች ውጪ አባትነት በፍርድ ቤት ውሣኔ ሊታወቅ አይችልም።

<u>ክፍል **2**</u>

<u>አባትነት በመወሰን ላይ ስለሚኖረው የሕግ ግጭት</u>

አንቀጽ **1)81** <u>አባትነት ስለመወሰን **/1/** መሠረቱ</u>

አባትነትን ስለመወሰን ከዚህ በላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተፈፃሚ በማድረግ አንድ ልጅ ከአንድ በላይ አባቶች አሉት ከተባለ የልጁ አባትነት በሕግ በሚሰጣቸው ሰዎች መካከል በሚደረግ ስምምነት ሊወሰን ይችላል።

አንቀጽ **1)82** <u>ሥርዓት (ፎርም)</u>

1 የአባትነትን ውሣኔ የሚሰጠውን ስምምነት ሦስት ምስክሮች ሊያረጋግጡትና ፍርድ ቤት ሊያፀድቀው ይገባል።

2 ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር የልጁን እናት ቃል መስማት ይገባል።

አንቀጽ **1)83** <u>የሕግ ግምት</u>

ስለአባትነት በሚደረገው ክርክር ስምምነት ያልተገኘ እንደሆነና አስፈላጊ ሆነ ከተገኘ ከዚህ ቀጥለው ያሉትን ሁለት የሕግ ግምቶች በመከተል ይፈፀማል።

ሀ) ጋብቻ ሳፈጸም እንደ ባል ከሚኖር ሰው ይልቅ ሕጋዊ ባል ይመረጣል።

ለ) ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ ከነበረው ባል ወይም ከሴትዋ ጋር አብሮ ይኖር ከነበረው ሰው ይልቅ እናቲቱ ልጁን ስትወልድ የነበራት ባል ወይም አብሮ የሚኖር ሰው የልጁ አባት ነው ማለት ይገባል።

አንቀጽ **1)84** <u>አባትነትን በስምምነት ስለማስተላለፍ</u>

1 ልጁ የተወለደው ጋብቻው ከተፈፀመ ወይም ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ከተጀመረ አንስቶ በ 2)! ቀናት ውስጥ የሆነ እንደሆነ ባልየው ወይም ከሴትየዋ ጋር እንደባል አብሮ የሚኖረው ሰው የልጁ አባት እኔ ነኝ ለሚል ሌላ ሰው በስምምነት አባትነቱን ሊያስተላልፍለት ይችላል።

2 እንዲሁም ልጁ ከጋብቻው መፍረስ ወይም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖሩ ከተቋረጠበት ቀን በኋላ 2)! ቀኖች አላልፎ ተወልዶ እንደሆነ ባልየው ወይም እንደባል አብሮ የኖረው ሰው ከዚህ በላይ የተነገረው መብት ይኖራል።

አንቀጽ ፭፪፭ ሥርዓት (ፎርም)

፩ በስምምነት የሚደረግ አባትነትን የማስተላለፍ ድርጊት ሦስት ምስክሮች ሊያረጋግጡትና

ፍርድ ቤት ሊያፀድቀው ይገባል።

፪ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር የእናቲቱ ቃል መስማት አለበት።

አንቀጽ ፭፪፭፯ <u>ስለወኪልነት</u>

፩. በዚህ ክፍል የተመለከቱት ስምምነቶች አካለ መጠን የደረሱና በፍርድ ያልተከለከሉ ባለጉዳዮች ራሳቸው መጨረስአለባቸው።

፪ስምምነቱ ሌላ ሰው እንዲያከናውኑለት ማድረግ የሚቻለው በፍርድ ቤት የፀደቀ ልዩ የውክልና ሥልጣን በመስጠት ብቻ ይሆናል።

አንቀጽ ፭፪፯ ቃልን ስለመሻር

አባትነትን በስምምነት የመወሰን ወይም የማስተላለፍ ድርጊት ሊሻር አይችልም።

አንቀጽ ፭፪፰ ስለማፍረስ

፩.ልጅነትን ለመቀበል የተደረገ ስምምነት በኃይል ድርጊት የተሰጠ መሆኑን በማስረዳት ሊፈርስ ይችላል።

፪. ልጄ ነው ብሎ ከተቀበለው ሰው ሊፀነስ የማይቻል ለመሆኑ በማያሻማ አኳኋን ካልተረጋገጠ በስተቀር ልጅነት የመቀበሉ ስምምነት በስህተት ወይም በማታለል የተደረገ ነው በማለትሊፈርስ አይችልም።

ክፍል ፫

ስለ ልጅነት ማስረጃ

አንቀጽ ፭፪፱ የልደት የምስክር ወረቀት

በአባትነት ወይም በእናትነት በኩል የአንድ ሰው ልጅነት የእገሌ ልጅ ነው የሚል የልደት ምስክር ወረቀት በማቅረብ ይረጋገጣል።

አንቀጽ ፭፫፡ የልደት የምስክርወረቀት በሌለ ጊዜ ስለሚቀርብ ማስረጃ

የልደት ምስክር ወረቀት የሌለ እንደሆነ የልጅነት ሁኔታ በመኖሩ ልጅነት ይረጋገጣል።

አንቀጽ ፭፫፩ የልጅነት ሁኔታ መኖር ትርጓሜ

አንድ ሰው የልጅነት ሁኔታ አለው የሚባለው በማህበረሰቡ ዘንድ የእርሱ ወይም የእርሷ ልጅ ነው እየተባለ የሚገመት ሲሆን ነው።

አንቀጽ ፭፫፪ ልጅነትን በልጅነት ሁኔታ ስለማስረዳት

፩. ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ መሠረት የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ለማስረዳት የተቻለ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ልጁ ነው ሲል የሕግ ግምት ይወስዳል።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው ግምትልጁ የተባለው ሰው ልጅሊሆን እንደማይችል በማስረዳት ማፍረስ ይቻላል።

አንቀጽ ፭፪፩፫ <u>ተወላጅነትንለማስረዳት ስለሚቀርብ ክስ</u>

፩. የልጅነት ሁኔታ የሌለ እንደሆነ ተወላጅነትን በምስክሮች ወይም በማናቸውም ዓይነት ማስረጃበማቅረብማስረዳት ይቻላል።

፪ ተወላጅነትን የማረጋገጥ ክስ ፍርድ ቤቱ ካልፈቀደው በስተቀር ሊቀርብ አይችልም።

፫. ተወላጅነትን ለማረጋገጥለሚቀርብክስ ፈቃድ የሚሰጠው ፍርድ ቤቱ ክሱን እንዲቀበል የሚያደርጉ ተጨባጭነት ካላቸው ተግባራት የሚመነጩ ግምቶች ወይም ምልክቶች ሲኖሩ ብቻ ነው።

አንቀጽ ፭፪፩፬ <u>ስለክሳሽ</u>

፩. ተወላጅነትን ለማረጋገጥ ክስ ለማቅረብ የሚችሉት ልጅ ወይም አሳዳሪ ወይም ወራሾቹ ናቸው።

3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የልጅ አባት ወይም እናት ነን የሚሉት ሰዎች ክስ ለማቅረብ ይችላሉ።

አንቀጽ ፭፪፩፭ ክስን ስላለመቀበል

ተወላጅነቱን ለማረጋገጥ የሚፈልገው ሰው ስለመወለዱ ከተሰጠው የልደት ምስክር ወረቀት ጋር የሚስማማ የልጅነት ሁኔታ ያለው እንደሆነ ከሌላ ሰው ተወላጅነቱን ለማረጋገጥ ክስ ለማቅረብ አይፈቀድለትም።

አንቀጽ ፭፪፩ **6** <u>ስለተከሳሽ</u>

፩. ተወላጅነትን ለማረጋገጥ ክሱን ያቀረበችው እናት ነኝ የምትል ሴት በሆነች ጊዜ ክስ

የሚቀርበው በልጁ ላይ ነው።

፪ ሆኖም ክሱ የቀረበው በሌላ ሰው ሲሆን ክሱ የሚቀርበው እናት ነች በተባለችው ወይም በወራሾቿ ላይ ነው።

አንቀጽ ፭፱፯ ክስ ስለሚቀርብበት ጊዜ

፩. ልጁ በህይወት እስካለ ድረስ ተወላጅነትን ለማረጋገጥ ክስ ለማቅረብ ይቻላል።

፪. የልጁ ወላጆች ወይም አሳዳሪዎች ልጁ አካለ መጠን ባልደረሰበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር ክስ ለማቅረብ አይችልም።

፫. ልጁ ፭ ዓመት ሳይሞላው የሞተ እንደሆነ እርሱ ከሞተ በኋላ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር ወራሾቹ ክስ ለማቅረብ አይችሉም።

ክፍል ፬

በተወላጅነት ላይ ስለሚነሳ ክርክርና ስለመካድ

ንዑስ ክፍል ፩

በተወላጅነት ላይ ስለሚነሳ ክርክር

አንቀጽ ፭፱፭ *መሠረቱ* በእናት በኩል ያለው ተወላጅነት በማንኛውም ባለጉዳይ በማንኛውም ጊዜ ሁሉ ክርክር ሊደረግበት ይችላል።

አንቀጽ ፭፱፮ ክስ ስለመቀበል

፩. በተወላጅነት ላይ ስለሚደረገው ክርክር የሚቀርበውን ክስ ፍ/ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሊቀርብ አይችልም፣

፪. በተወላጅነት ላይ ክርክር ለማድረግ ለሚቀርበው ክስ ፈቃድ የሚሰጠው ፍ/ቤቱ ክሱን እንዲቀበል የሚያደርጉት ተጨባጭነት ካላቸው ተግባራት የሚመነጩ ግምቶች ወይም ምልክቶች ሲኖሩ ብቻ ነው።

አንቀጽ ፭፱፯ ክስን ስላለመቀበል

ልጁ ተወላጅነቱን የሚያረጋግጥ የልደት የምስክር ወረቀትና ከዚሁ ጋር የሚስማማ የልጅነት ሁኔታ ያለው እንደሆነ በተወላጅነት ላይ ለማከራከር ፈቃድ አይሰጥም።

አንቀጽ ፭፱፰ ስለተከሳሽ

፩. በተወላጅነት ምክንያት የሚቀርበው ክስ በተወላጅነቱ ላይ ክርክር በተነሳበት ሰው ላይ ወይም በወራሾቹ ላይ ይመሰረታል።

፪. የልጁን እናት አስፈላጊ ሆነ ሲገኝም የልጁን አባት ክርክሩ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ አስፈላጊ ነው

ንዑስ ክፍል ፪

ስለመካድ

አንቀጽ ፭፻፹፪ *መሠረቱ*

በአባት በኩል ያለን መወለድ መቃወም የሚችለው የመካድ ክስ በማቅረብ ብቻ ነው።

አንቀጽ ፭፻፹፫ *ከልጁ እናት ጋር የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ስላለመኖር /፭/ መሠረቱ*

የልጁ አባት ነህ ተብሎ በህግ አባትነት የሚሰጠው ሰው ልጁ ከመወለዱ በፊት በሶስት መቶኛውና በአንድ መቶ ሰማንያኛው ቀናት መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ከልጁ እናት ጋር የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ላለመፈፀሙ በማያጠራጥር ሁኔታ ያስረዳ እንደሆነ የተባለውን ልጅ ልጄ አይደለም ለማለት ይችላል።

አንቀጽ ፭፻፹፬ *የህግ ግምት*

፭. ከሁለቱ አንዱ ባቀረበው የመፋታት ጥያቄ መሠረት ወይም በሁለቱ መካከል በተደረገው የመለያየት ስምምነት ምክንያት ባልና ሚስቱ በእውነት ተለያይተው በነበሩበት ጊዜ በመካከላቸው የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት እንዳልተደረገ ይገመታል።

፪. ለዚህ ተቃራኒ ሆኖ የሚቀርበው ማስረጃ በማንኛውም ምክንያቶች ቢሆን ይሰማል።

አንቀጽ ፭፻፹፭ *አባት ለመሆን ስለአለመቻሉ /፭/ መሠረቱ*

በህግ የልጅ አባት ነህ የተባለው ሰው የዚሁ ልጅ አባት ሊሆን አለመቻሉን በማጠራጥር አኳኋን ባስረዳት ለመካድ ይችላል።

አንቀጽ ፭፻፹፮ *ክስን ለመቀበል ስለመቻል*

፭. ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ መሠረት የሚቀርበው የመካድ ክስ ፍ/ቤት ካልፈቀደ በቀር ሊቀርብ አይችልም።

፪. ፈቃዱም የሚሰጠው ፍ/ቤት ክሱን እንዲቀበል የሚያደርገው በቂና አስተማማኝ ከሆነ መረጃ የሚመነጭ የህሊና ግምት ወይም ከባድ ምልክት ሲኖር ብቻ ነው።

አንቀጽ ፭፻፹፯ *ስለ ህሊና ግምቶችና ከባድ ምልክቶች*

፭. የህሊና ግምቶችና ከባድ ምልክቶች የሚባሉት ልጅህ ነው ከተባለው ሰው አባትነት ጋር የማይስማሙ ለመሆናቸው በሳይንስ ዕውቀት ተለይተው የሚታዩ ተጨባጭ መረጃዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

፪. እንዲሁም እነዚህ ነገሮች ሴቲቱ በሰውየው አባትነት ላይ ጥርጣሬ በሚያሳድር አኳኋን የልጅን መወለድ እርግዝናዋን ከሰውየው የደበቀችበት ድርጊት ሊመነጩ ይችላሉ።

አንቀጽ ፳፻፹፰ <u>ስለሴሰኝነት በባል ላይ የሚደረግ ዝሙት ወይም ስለእናቲቱ ማመን</u>

እናቲቱ በባሏ ላይ ያደረገችው ሴሰኝነት /የዝሙት/ ስራ ወይም ልጁ የሌላ ሰው ስለመሆኑ፣የምትሰጠው የእምነት ቃል ብቻ እንደ ከባድ ምክንያት ሊቆጠሩ አይችሉም።

አንቀጽ ፳፻፹፱ <u>ስለከሳሽ</u>

፳. የእኔ ልጅ አይደለም ብሎ የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚችለው የልጅ አባት ነህ ተብሎ የህግ ግምት የሚሰጠው ሰው ብቻ ነው።

፪. በዚህ ጉዳይ ላይ በተለይ እናቲቱ፣ አባት ነኝ ባዩ፣ ዐቃቤ ህግ ወይም ልጁ ራሱ ክስ ሊያቀርቡ አይችሉም።

አንቀጽ ፳፻፺ <u>በፍርድ ቤት የተከለከለው ሰው</u>

፳ በፍርድ የተከለከለው ሰው ፍርድ ቤትን በማስፈቀድ የመካድ ክስ ሊያቀርብ ይችላል።

፪. እንዲሁም በፍርድ የተከለከለው ሰው አሳዳሪው ይህንኑ የፍርድ ቤት ፈቃድ ከተቀበለ በኋላ በፍርድ በተከለከለው ሰው ስም መካድ ክስ ለማቅረብ ይችላል።

አንቀጽ ፳፻፺፳ <u>የመካድ ክስ ስለሚቀርብበት ጊዜ /፳/ መሠረቱ</u>

፳. የእኔ ልጅ አይደለም የሚል የመካድ ክስ የልጁን መወለድ ካወቀበት ወይም ማወቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ ባሉት ፳፻፹ ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት።

፪. እናትነት የተወሰነው ተወላጅነትን ለማረጋገጥ ለቀረበ ክስ ሲሆን የመካድ ክስ የሚቀርበው ተወላጅነትን ለማረጋገጥ የቀረበውን ክስ የሚወስን የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ ጀምሮ ባሉት ፳፻፹ ቀናት ነው።

አንቀጽ ፳፻፺፪ <u>ልዩ ልዩ ሁኔታ</u>

፳. በህግ ግምት የልጁ አባት ነው የሚባለው ሰው የሞተ ወይም የመካድ ክስ ለማቅረብ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ችሎታውን ያጣ እንደሆነ ከተወላጆቹ አንዱ በርሱ ፈንታ ሆኖ የመካድ ክስ ሊያቀርብ ይችላል።

፪. ተወላጆቹ የሌሉ እንደሆነ አባትና እናቱ እነዚህ የሌሉ እንደሆነ ወደ ላይየሚቆጠሩ ወላጆቹ

አንዱ መብቱን ሊሰራበት ይችላል።

፫. ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆቹ የሌሉ እንደሆነ የተባለውን መብት ማናቸውም ሌላ ወራሽ

ወይም ወኪል ሳይጨመር ከወንድሞቹ ወይም እህቶቹ አንዱ ሊሰራበት ይችላል።

አንቀጽ ፭፻፶፫ ክስን ስላለመቀበል

ባልየው በጽሁፍ በሰጠው ፈቃድ መሰረት ልጁ በሰው ሰራሽ ዘዴ የተፀነሰ ስለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም።

አንቀጽ ፭፻፶፬ ስለተከሳሾች

፩. የመካድ ክስ በልጁ ላይ እርሱም ሞቶ እንደሆነ በወራሾቹ ላይ ይቀርባሉ።

፪. የልጁ እናት በሚቀርበው ክስ ውስጥ እንድትገባ ማድረግ ያስፈልጋል።

፫. ልጁ አካለ መጠን ያልደረሰ ከሆነ ፍርድ ቤት በተለይ የመረጠው ተጠባባቂ ሞግዚት ወኪል ይሆንዋል።

ምዕራፍ አስራ አንድ

ስለጉዲፈቻ

አንቀጽ ፭፻፶፭ ስለጉዲፈቻ ዝምድና መሠረቱ

በአንድ ሰውና በአንድ ልጅ መካከል በሚደረግ ስምምነት የጉዲፈቻ ዝምድና ሊፈጠር ይችላል።

አንቀጽ ፭፻፶፮ ውጤቱ

ከዚህ በታች በአንቀጽ ፭፻፶፯ በተመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የጉዲፈቻ ልጅ በማናቸውም ረገድ ቢሆን እንደጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ ይቆጠራል።

አንቀጽ ፭፻፶፯ ልዩ ሁኔታ

፩. የጉዲፈቻ ስምምነት በግልጽ የተቃወሙት ወደ ላይ በሚቆጠሩ ወላጆች ወይም ወደ ጎን የሚቆጠሩ ዘመዶችን በሚመለከት ውጤት አይኖረውም።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው ተቃውሞ ስምምነቱ በፍርድ ቤት መጽደቁን ካወቁ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ በፍርድ ቤት መዝገብ ካልተመዘገበ በቀር አይፀናም።

አንቀጽ ፩፻፺፰ የጉዲፈቻ ልጅ ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር ስለሚኖር ግንኙነት

፩. የጉዲፈቻ ልጅ ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር ያለው የዝምድና ግንኙነት እንደተጠበቀ ይቆያል።

፪. የጉዲፈቻ ልጅየው ሚስት ባል እና ተወላጆችም ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር የዝምድና ግንኙነት ይኖራቸዋል።

፫. በቀደምት ቤተሰቦቹና በጉዲፈቻ ቤተሰቦቹ መካከል መምረጥ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ለጉዲፈቻ ቤተሰቦቹ ቅድሚያ ይሰጣል።

አንቀጽ ፩፻፺፺ የጉዲፈቻ አድራጊው ዕድሜ

፩.ዕድሜው ከ፳፭ አመት ያላነሰ ማንኛውም ሰው የጉዲፈቻ አድራጊ ሊሆን ይችላል።

፪. የጉዲፈቻ አድራጊዎች ባልና ሚስት በሆኑ ጊዜ የአንዳቸው ዕድሜ ፳፭ አመት

የሞላ ከሆነ በቂ ነው።

አንቀጽ ፪፻ የጉዲፈቻ ልጅ ዕድሜ

ዕድሜው ከአስራ ስምንት ዓመት በታች የሆነና ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ያልወጣ ማናቸውም ሰው የጉዲፈቻ ልጅ ለመሆን ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፩ ያገባ ሰው ስለሚያደርገው የጉዲፈቻ ስምምነት

፩ የጉዲፈቻ አድራጊውያገባ በሚሆንበት ጊዜ፣ባልና ሚስቱ በጋራ ልጁንየጉዲፈቻ ልጃቸው

የሚያደርጉት ካልሆኑ በቀር የጉዲፈቻ ስምምነት ለማድረግ አይችሉም።

፪. የጉዲፈቻ ልጅ፣የጉዲፈቻ አድራጊ ባል ወይም ሚስት ልጅ በሆነ ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተውን ድንጋጌ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

፫. እንዲሁም ከባል ወይም ከሚስት አንደኛው ፈቃድ ለመስጠት የማይችል ከሆነ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው ተፈፃሚነት አይኖረውም።

አንቀጽ ፪፻፪ የተፀነሰ ልጅ የጉዲፈቻ ልጅ ስለማድረግ

፩. የተፀነሰን ልጅ የጉዲፈቻ ልጅ ማድረግ ይቻላል።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው ድንጋጌ ቢኖርም ልጁ በተወለደበስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ እናቲቱ ስምምነቱን በገዛ ፈቃዷ ለመሰረዝትችላለች።

አንቀጽ ፪፻፫ <u>ስለ ጉዲፈቻ አድራጊው ልጆች</u>

፩ የጉዲፈቻ አድራጊው ከአብራኩ የተገኙ ልጆች ያሉት መሆኑ የጉዲፈቻ ስምምነት ከማድረግ የሚያግደው አይሆንም።

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው ድንጋጌ ቢኖርም ፍርድ ቤቱ የጉዲፈቻ ስምምነቱ ከማጽደቁ አስቀድሞ የጉዲፈቻ አድራጊው ከአብራኩየተገኙ ልጆች ያሉት መሆኑ በጉዲፈቻ ልጅ መልካም አስተዳደግና ጥቅምላይ ሊኖር የሚችለውን ተጽዕኖ ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

አንቀጽ ፪፻፬ <u>አንድ ልጅ ከአንድ በላይ የጉዲፈቻ አድራጊ ሊኖረው የማይችል ስለመሆኑ</u>

፩. ባልና ሚስት ካልሆኑ በቀር ማንኛውም ልጅ ለብዙ ሰዎች የጉዲፈቻ ልጅ ሊሆን አይችልም።

፪. ጉዲፈቻ አድራጊው የሞተ እንደሆነ ግን አዲስ የጉዲፈቻ ስምምነት ለማድረግይቻላል።

፫. ልጅየው የባልና ሚስት የጉዲፈቻ ልጅ ከሆነና ከባልና ሚስቱ አንደኛው የሞተእንደሆነ በህይወት ካለው ሰው ጋር የሚጋባው አዲስ ተጋቢ የጉዲፈቻ ልጅ ሊያደርገው ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፭ <u>ስምምነቱን ስለሚያደርጉ ወገኖች</u>

የጉዲፈቻ ስምምነት በጉዲፈቻ አድራጊውና በልጁ አሳዳሪ መካከል ይደረጋል።

አንቀጽ ፪፻፮ <u>የጉዲፈቻው ልጅ ወላጆች ፈቃድ</u>

፩. የልጁ እናትና አባት በሕይወት ያሉና የታወቁ ከሆነ ልጁ የጉዲፈቻ ልጅ እንዲሆን ፈቃዳቸውን እንዲሰጡ ያስፈልጋል።

፪. ከወላጆች አንደኛው የሞተ፣የጠፋ፣የማይታወቅ እንደሆነ ወይም ፈቃዱን ለመስጠት የማይችል ሲሆን ሌላኛው ወላጅ ፈቃዱን ይሰጣል።

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገገው ቢኖርም ከወላጆቹ አንዱ ፈቃዱን ለመስጠት ያልፈለገ እንደሆነና የልጁ ዕድሜ ፲ 6 አመትና ከዚያ በላይ ከሆነ ፍርድ ቤት የአንድን ወላጅ ፈቃድና የልጁን አስተያየት በመጠየቅ የጉዲፈቻ ስምምነት ሊያፀድቀው ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፯ ስለመንግስት ወይም የግል እንለማለውታን አሳዳጊ ተቋሞች

፩ የመንግስት ወይም የግል እንለማለውታን አሳዳጊ ተቋሞች እያሳደጉት ያሉትንማንኛውንም ልጅ ለጉዲፈቻ አድራጊዎች በስምምነት ለመስጠት ይችላሉ።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከቱት ተቋሞች አንዱ ልጅ በስምምነት ከመስጠታቸው በፊት የህፃናት ደህንነት ለመከታተል ስልጣን ለተሰጠው የመንግስት አካል ስለልጁ ማንነት፣በምን ሁኔታ ተቋሙ እንደተረከበውና ስለጉዲፈቻ አድራጊው ግላዊ፣ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አቋም መግለጫ ማቅረብ አለባቸው።

አንቀጽ ፪፻፰ የፍርድ ቤቱ ሥልጣን

፩. የጉዲፈቻ ስምምነት ፍርድ ቤት ካላፀደቀው በስተቀር ውጤት አይኖረውም።

፪. ፍርድ ቤቱ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ከማጽደቁ አስቀድሞ በወሳኝ መልኩ ለልጁመልካም አስተዳደግና ጥቅም የሚበጅ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

፫. ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፪፻፯ እና ፪፻፰ የተመለከቱት እና የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤት የጉዲፈቻ ስምምነቱን ከማጽደቁ በፊት የሚከተሉትን ከግምት ማስገባት አለበት፤

ሀ/ ልጅየው ስለጉድፈቻ ስምምነት ያለውን አስተያየት፣

ለ/ አስቀድሞ ፈቃድ ያልተሰጠ ከሆነም የአሳዳሪውን አስተያየት፣

ሐ/ የጉዲፈቻ አድራጊው ልጁን ለማሳደግና ለመንከባከብ ያለው ብቃት፣

መ/ ጉዲፈቻ አድራጊው እንደ ልጁ አድርጎ እንደሚያሳድገውናአለአግባብ መጠቀሚያ

እንደማያደርገው ለመገመት የሚያስችልመረጃ መኖሩን።

አንቀጽ ፪፻ 9 የጉዲፈቻ ስምምነት የማይሰረዝ ስለመሆኑ፡-

፩.የጉዲፈቻ ስምምነት በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /፪/ ከተመለከተው ሁኔታ ውጪ ሊሰረዝ አይችልም።

፪. የጉዲፈቻ አድራጊው በጉዲፈቻ የተቀበለውን ልጅ እንደልጁ በማሳደግ ፈንታበባርነት ወይም ባርነትን

በሚመስል ሁኔታ ወይም ከግብረገብ ውጭ በሆነ ተግባሮችእንዲሰማራ በማድረግ መጠቀሚያ

ያደረገውእንደሆነ ወይም በማናቸውም ሌላመንገድ የልጁን የወደፊት ህይወት ክፋኛ በሚጎዳ አኳኋን

የያዘው መሆኑን የተረዳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ለመሰረዝ ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፲. የጉዲፈቻ ስምምነት እንዲሰረዝ አቤቱታ ስለማቅረብ

፩. የጉዲፈቻ ልጅ ራሱ የሕጻናትን ደህንነት ለመከታተል ሥልጣን የተሰጠውየመንግስት አካል በጉዳዩ

ያገባኛል የሚል ማንኛውም ሰው ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ የተደነገገውን መሰረት በማድረግ

የጉዲፈቻ ስምምነት እንዲሰረዝአቤቱታ ለማቅረብ ይችላል፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት አቤቱታ ሲቀርብለት ፍርድ ቤቱጉዲፈቻ አድራጊውን

ከማስቀረቡ በፊት ለአቤቱታ ምክንያት ናቸው የተባሉትንመረጃዎች እውነት ሆነው ቢገኙ የጉዲፈቻ

ስምምነቱን ለማፍረስ በቂ መሆናቸውንማረጋገጥ አለበት።

ምዕራፍ አስራ ሁለት

ቀለብ መስጠት ግዴታ

አንቀጽ ፪፻፲ 1 ስለግዴታው ይዘት

በዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፲ 2 ድንጋጌዎች መሰረት ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው እንደ ባለጉዳዮቹ ሁኔታና እንደ አካባቢው ልማድ የሚስማማውንበመከተል ለቀለብ ተቀባይ ምግብ፣ መኖሪያ፣ልብስ፣ ጤናን የሚጠብቅበትናእንደሁኔታው ለትምህርት አስፈላጊ የሆነውን ነገር መስጠት አለበት።

አንቀጽ ፪፻፲ 2 ግዴታው በእነማን መካከል ስለመሆኑ

፩. በዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፲ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀለብ የመስጠት ግዴታ

የሚኖረው በቀጥታ ወላጆችና ተወላጆች ወይም በቀጥታ የጋብቻ ዘመዳሞች መካከል ነው።

፪. እንዲሁም ወንድማማቾችና እህትማማቾች በሆኑት መካከል ቀለብ የመስጠት ግዴታ ይኖራል።

አንቀጽ ፪፻፲ 3 ግዴታ ስለሚቀርበበት ሁኔታ

ጋብቻው የፈረሰው በሞት ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በጋብቻ ዘመዶች መካከል ያለው ቀለብ የመስጠት ግዴታ ቀሪ ይሆናል።

አንቀጽ ፪፻፲፬ ቀለብ ተቀባዩ መብቱን ስለሚያጣበት ሁኔታ

ቀለብ ተቀባዩ በቀለብ ሰጪው ወይም በዚህ ሰው ወደ ላይና ወደታች በሚቆጠሩ ወላጆች ወይም ተወላጆች ወይም ባል ወይም ሚስት ህይወት ወይም ንብረት ላይ የወንጀል ተግባር የፈጸመ ወይም ለመፈጸም የሞከረ ስለመሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ቀለብ የመቀበል መብቱን ያጣል።

አንቀጽ ፪፻፲፭ ግዴታው እንዲኖር አስፈላጊ ሁኔታዎች

ቀለብ የመስጠት ግዴታ ተፈጻሚ የሚሆነው ቀለብ ጠያቂው ሠርቶ ለመኖር አስፈላጊ የሆነ ገቢ ለማግኘት አቅም የሌለው ወይም የመስራትአቅም ቢኖረውም ሥራ ማግኘት ያልቻለና በችግር ላይ የሚገኝ ሲሆን ብቻ ነው።

አንቀጽ ፪፻፲፯ስለግዴታው አፈጻፀም

፩. በመሠረቱ ቀለብ የመሰጠት ግዴታ የሚፈጸመው ቀለብ ሰጪው ለቀለብ ተቀባዩ የቀለቡን ገንዘብ በመስጠትነው።

፪. የቀለቡ መጠን የሚወሰነው ቀለብ ጠያቂው ያለበትንችግር እና የቀለብ ሰጪውን አቅም በማመዛዘን ነው።

አንቀጽ ፪፻፲፰ ሁኔታውን ማሻሻል የሚቻል ስለመሆኑ

ቀለብ ሰጪው ወይም ተቀባዩ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ስለቀለቡ መጠን ወይም ስለቀለቡ ተቀባዩ መኖሪያ የተሰጠውን ውሳኔ በማናቸውም ጊዜ ማሻሻል ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፲፱ ቀለቡ ስለሚከፈልበት ሁኔታ

ቀለቡ የሚከፈለው በተቻለ መጠን ለቀለብ ተቀባዩ በሚያመቸው ቦታ ይሆናል።

አንቀጽ ፪፻፲ 9 የቀለብ ገንዘብ ሊተላለፍና ሊያዝ የማይቻል ስለመሆኑ

፩. ለቀለብ የሚከፈል ገንዘብ ሊተላለፍ ወይም ሊያዝ አይችልም።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገገው ቢኖርም ለቀለብ የሚከፈል ገንዘብ የሚከፈልበት ጊዜ

ከመድረሱ አስቀድሞ ቢሆንም እንኳ ቀለብ ተቀባዩ ላለበት ችግር አሳቢ ለሚሆኑ ለዕርዳታ ለተቋቋሙ

ድርጅቶች ሊተላለፍ ይችላል።

፫. እንዲሁም ለቀለብ ተቀባይ ኑሮ አስፈላጊ የሆነውን ነገር ያበደሩት ሌሎች ሰዎች በተመለከተ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ድንጋጌተፈጻሚነት አይኖረውም።

አንቀጽ ፪፻፳ የቀለብ ገንዘብ የማይጠራቀም ስለመሆኑ

ቀለብ ተቀባዩ ለኑሮው አስፈላጊ መሆኑን ካላረጋገጠ በቀርቀለቡን ገንዘብ በመቀበል ካለበት ቀን ጀምሮ በተከታዮቹ ሦስት ወራት ውስጥ ያልተቀበለው ይም ሳይጠይቀው የቀረ እንደሆነ የተጠራቀመ ቀለብ እንዲሰጠውመጠየቅ አይችልም።

አንቀጽ ፪፻፳፩ ቀለብ ተቀባዩን በቀለብ ሰጪው ቤት ለማኖር ስለመቻል

፩. ቀለብ ሰጪው ቀለብ ተቀባዩን በመኖሪያ ቤቱ ተቀብሎበማቀመጥ ቀለብ የመስጠት ግዴታውን ሊፈጽምይችላል።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ስለተመለከተው ጉዳይክርክር የተነሳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የነገሩን የአካባቢሁኔታዎች በመመልከት ተገቢ መስሎ የታየውን ይወስናል።

፫. ቀለብ ሰጪው ቀለብ ተቀባዩን በመኖሪያ ቤቱ እንዲያስቀምጥ ምን ጊዜም ቢሆን አይገደድም።

አንቀጽ ፪፻፳፪ <u>ስለቀለብ ሰጪዎች ብዛት /፩/ መሠረቱ</u>

ስለቀለብ ተቀባዩ ቀለብ የመሰጠት ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ብዙ የሆኑ እንደሆነ ከእነርሱ መካከል አንዱ ቀለቡንእንዲሰጠው ሊጠይቀው ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፳፫ <u>ስለአቤቱታ</u>

፩. ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ብዙ ሆነውከእነርሱ መካከል አንዱ ወይም ከዚያ በላይ

የሆኑትቀለቡንየከፈሉ እንደሆነ ሳይከፍሉ የቀሩት ድርሻቸውንእንዲከፍሏቸው መጠየቅ ይቻላል።

፪. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ /፩/ ስለተመለከተው ጉዳይ ክርክር የተነሳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ

ተከሳሾቹ ያላቸውንሀብትና ከከሳሽ ጋር ያላቸውን የሥጋ ወይም የጋብቻዝምድና ደረጃ በማመዛዘን

ተከሳሾቹ የቀለቡን ገንዘብበሙሉ ወይም በከፊል እንዲከፍሉ ሊወስንባቸውይችላል።

አንቀጽ ፪፻፳፬ <u>ለቀለብ ሰጪዎች የሚሰጥ ከፋይነት ተራ</u>

በዚህ ኅግ አንቀጽ፪፻፲ 2 መሠረት ቀለብ የመስጠትግዴታ ያለባቸው ሰዎች ቅደም ተከተል

ሀ/ በመጀመሪያ ደረጃ ባል ወይም ሚስት

ለ/ በሁለተኛ ደረጃ ተወላጆች እንደየደረጃቸው

ሐ/ በሦስተኛ ደረጃ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች እንደየደረጃቸው

መ/ በአራተኛ ደረጃ ወንድማማቾችና እህትማማቾች

ሠ/ በአምስተኛ ደረጃ የጋብቻ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች እንደየደረጃቸው

አንቀጽ ፪፻፳፭ <u>በጋራ ቀለብ ሰጪዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት</u>

፩. የጋራ ቀለብ ሰጪዎች እርስ በእርሳቸው ስላላቸው ግንኙነት ለጋራ ቀለብ ተቀባያቸው ከእነርሱ መካከል አንዱ ቀለቡን እንዲሰጠው በማለት የሚፀና ስምምነት ለማድረግ ይችላሉ።

፪. ቀለብ ተቀባይ ስምምነቱን ወዶ የተቀበለ እንደሆነ ይህንን ስምምነት የሚያከራክርበት ከባድ ምክንያት ካልተገኘ በቀርቀለቡን ከሌሎች ቀለብ ሰጪዎች መጠየቅ አይችልም።

አንቀጽ ፪፻፳፯ ስለጉዲፈቻ ልጅ ልዩ ሁኔታ

፩. የጉዲፈቻ ልጅ ባል ወይም ሚስትና የቀጥታ መስመር ተወላጆች የጉዲፈቻ አድራጊው ቤተዘመዶች ቀለቡን መስጠት በማይችሉበት ሁኔታ ካልተገኙ በቀር የሥር ወላጆቹን ቤተዘመዶች ቀለብ ለመጠየቅ አይችሉም።

፪. የቀደምት ቤተሰቦቹ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ቀለብ ለማግኘት ከዘመዳቸው አንዱን ለመጠየቅ የማይችሉ ካልሆነ በቀር በጉዲፈቻ የሰጡትን ልጅ ቀለብ ሊጠይቁት አይችሉም።

አንቀጽ ፪፻፳፯፩ስለ ሥርዓተ ቀብር ወጪ

፩. ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው ለዚህ ለተባለው ሰው ሥርዓተ ቀብር የወጣውን ወጪ ለመክፈል ይገደዳል።

፪. ይህን ወጪ ያደረገው ሰው ወጪውን እንዲተካለት ቀለብ ቀለብ ሰጪውን ለመጠየቅ ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፳፰ልዩ ስምምነቶች

ልዩ ስምምነቶች በማድረግ በዚህ ምዕራፍ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ለመለወጥ አይፈቀድም።

ምዕራፍ አስራ ሶስት

አካለ መጠን ስላልደረሱ ሰዎች

ክፍል ፩

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

አንቀጽ ፪፻!9 ትርጓሜ

አካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ማለት ዖታ ሳይለይ ዕድሜው አስራ ስምንት ዓመት ያልሞላው ልጅ ነው።

አንቀጽ ፪፻፴ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ የሌለው ስለመሆኑ

፩. አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ስለ መልካም አስተዳደጉና ደህንነቱጉዳይ በአንድ አሳዳሪው እየተጠበቀ

ይቆያል።

፪. ንብረት ነክ ጥቅሞቹንና በአጠቃላይ የንብረቱን አስተዳደርበሚመለከት በሞግዚቱ ይወከላል።

፫. በሕግ በግልጽ ለተመለከቱት ጉዳዮች ካልሆነ በስተቀር አካለ መጠንያልደረሰው ሰው ሕጋዊ ድርጊቶችን ለመፈጸም አይቻልም።

አንቀጽ ፪፻፴፩ የዕድሜ ማስረጃ

፩. የአንድ ሰው ዕድሜ የሚያረጋግጠው በልደት ምስክር ወረቀት ነው።

፪. የልደት ምስክር ወረቀት የሌለ እንደሆነ ዕድሜውን በአስተማማኝነት ለማረጋገጥ ያስችላሉ በሚባሉ

ሠነዶች ወይም ከሁለት ያላነሱ መስክሮችንቃል መሠረት በማድረግ ፍርድ ቤት ዕድሜውን ይወስናል።

አንቀጽ ፪፻፴፪ ውሳኔ ሰጪ አካላት መከተል ስላለባቸው መርህ

በዚህ ምዕራፍ መሰረት ውሳኔ የሚሰጥባቸው ጉዳዮች ሁሉ ለልጆች ደህንነትና መልካም አስተዳደግ የሚበጁ መሆን ይኖርባቸዋል።

ክፍል ፪

አካለ መጠን ያልደረሰን ልጅ ስለሚጠብቁ ተቋሞች

አንቀጽ ፪፻፴፫ የወላጆች ሥልጣን

አባትና እናት ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ ሁሉ አካለ መጠን ላልደረሱትልጆቻቸው የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት የጋራ ሥልጣን አላቸው።

አንቀጽ ፪፻፴፬ ከወላጆቹ የአንዱ ብቁ አለመሆን

፩. ከወላጆቹ አንዱ የሞተ፣ ችሎታ ያጣ፣ የተጋቢነት መብት ያጣ፣ ወይምከቤተዘመድ አስተዳዳሪነት

መብቱ የታገደ እንደሆነ የአሳዳሪነትና ሞግዚትነት ሥልጣኑን ይዞ የሚቆየው አንደኛው ወገን ብቻ

ይሆናል።

፪. እንዲሁም የልጁ አባት ያልታወቀ በሆነ ጊዜ የዚህን ስልጣን ሥራ የምትፈጽመው እናቱ ብቻ

ትሆናለች።

አንቀጽ ፪፻፴፭የልጆቹ አባትና እናት መፋታት

፩. በዚህ ሕግ አንቀጽ ፹፯ መሠረት ባልና ሚስት በስምምነት ሲፋቱ የልጆቻቸውን አሳዳሪነትና

ሞግዚትነትን በተመለከተ በስምምነት ይወስናሉ።

፪በማናቸውም የፍቺ ሁኔታ የልጆቻቸውን አሳዳሪነትና ሞግዚትነት ባልና ሚስቱበስምምነት ሊወስኑ ካልቻሉ ፍቺውን የወሰነው ፍርድ ቤት ስለ ልጆቹ አሳዳሪናሞግዚትም አብሮ ይወስናል።

አንቀጽ ፪፻፴፮ በኑዛዜ ቃል የተመረጠ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት /መሠረቱ/

፩. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ በህይወት ያለው ወላጅ ከሞቱ በኋላ ልጁንየሚያስተዳድር ወይም ለልጁ ሞግዚት የሚሆነውን ሰው በመጨረሻ በኑዛዜ ቃል ለመምረጥ ይችላል።

፪. እንዲሁም የአሳዳሪውን ወይም ሞግዚቱን ሥልጣን ለመወሰንና አሳዳጊነቱንየሥራ አመራር ሥልጣን ለተወሰነ ሁኔታ ብቻ ለመስጠት ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፴፯ አሳዳሪው ወይም ሞግዚት ለመሾም የሚፈጸም ግዴታ

አባት ወይም እናት በሕይወት ሳለ አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ የአሳዳሪነትወይም ሞግዚትነት ሥራ ያካሂድ የነበረ ካልሆነና በዚሁም ጊዜ በገዛ ፈቃዱ ሥልጣኑን አውቆ የተወ ካልሆነ በስተቀር ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፪፻፴ 6 ለአባት ወይም ለእናት የተሰጠው መብት አይኖርም።

አንቀጽ፪፻፴፰ ለፍርድ ቤት አቤቱታ ስለማቅረብ

አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ጥቅም የሚያስገድድ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ስለአሳዳሪው ወይም ስለሞግዚቱ አባት ወይም እናቱ ያደረጉትን ውሳኔ ፍርድቤት ሊሽረው ወይም ሊያሻሽለው ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፴፱ የልጅን አሳዳሪነት ወይም ሞግዚትነት ስልጣን ሊይዙ የሚገባቸው ዘመዶቹ /፭/

ሊከተሉት የሚገባ ቅደም ተከተል

አንድ ልጅ አባትና እናት የሌለው እንደሆነና ከሁለቱ በመጨረሻ የሞተው ወላጅ በሚገባ ሁኔታ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ሳያደረግለት ቀርቶ እንደሆነ ለልጁ አሳዳሪነት ወይም ሞግዚትነት በሕጉ መሰረት የሚመረጡና ይህ ስልጣንየሚሰጣቸው ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ሰዎች ናቸው፡-

ሀ/ የልጁ ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች

ለ/ እነዚህ በሌሉ ጊዜ አካለ መጠን የደረሱ የልጁ ወንድሞች ወይም እህቶች

ሐ/ እነዚህ በሌሉ ጊዜ የልጁ አጎት ወይም አክስት።

አንቀጽ ፪፻፵ ይህ ቅደም ተከተል ስለሚለወጥበት ሁኔታ

፩. ከዚህ በላይ በተመለከተው መሰረትሥልጣን በሚሰጠው ሰው ምትክ ለልጁ የሥጋ ዝምድና ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ማንኛውም ሰው የአሳዳሪነቱ ወይም የሞግዚትነቱ ሥልጣን ይሰጠኝ ሲል ጥያቄ ለማቅረብ ይችላል።

፪. ይህም ጥያቄ መቅረብ የሚገባው ቅደም ተከተሉ ለሚመለከታቸው ዘመዶች ሲሆን ስምምነት ካልተገኘ ግን ጉዳዩ ለፍርድ ቤት ይቀርባል።

፫. ጥያቄው መቅረብ ያለበት አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ይህን ሥልጣን መያዙ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወር ውስጥ ይሆናል።

፬. ጥያቄውን ለመቀበል ወይም ላለመቀበል መሰረት የሚሆነው የልጁ ደህንነት ጥቅም ሊሆን ይገባል።

አንቀጽ ፪፻፵ 1 በህግ የሚመረጡ ዘመዶች መታጣት

፩. ከዚህ በላይ ባሉት አንቀጾች የተመለከተውን መሰረት በማድረግ ለልጁ አንድ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ለማግኘት ያልተቻለ እንደሆነ ይህን ሥራና ሥልጣን ፍርድ ቤት ለመረጠው ሰው ሊሰጥ ይችላል።

፪. ፍርድ ቤቱ ይህን ጉዳይ ለመወሰን የልጁ ዘመድ በሆነ ወይም ባልሆነው ያገባኛል ባይ በሚቀርብ ጥያቄ ሊመሠረት ይችላል።

፫. የሕጻናትን ደህንነት ለመከታተል ሥልጣን የተሰጠው የመንግስት አካልም ጉዳዩን ለፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፵፪ የፍርድ ቤት ምርጫ ፡ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመዶች

ፍርድ ቤት ለልጁ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት እንዲሆን የሚመረጠውና ይህን ሥልጣን የሚሰጠው የልጁ የቅርብ የሥጋ ዘመድ የሆነን ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለውና በተቻለም መጠን ይህን ሥራ ለማከናወን ችሎታና ፍቃደኝነት ያለውን ሰው ነው።አንቀጽ ፪፻፵፫/፪/ የበጎ አድራጎት ድርጅት

ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነቱን ሥልጣን ለዚህ ዓይነት ጉዳይ ለተቋቋመው የበጎ አድራጎት ድርጅት ሊሰጥ ይችላል።

አንቀጽ ነ፪፻፵፬ ተመሳሳይ ሁኔታዎች

ከዚህ በላይ ለተፃፉት ድንጋጌዎች አፈፃፀም አንድ ሰው በህግ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ተግባሮቹን ለማከናወን የማይችል እንደሆነ እንደሌለ ይቆጠራል።

አንቀጽ ፪፻፵፭ <u>የአሳዳሪው ወይም የሞግዚቱ መታወቂያ</u>

፩. በመሰረቱ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ አሳዳሪ እንዲሆን ሥልጣን ተሰጥቶት የልጁን አሳዳሪነት የተቀበለው ሰው ሞግዚቱም ነው።

፪. የነገሩ ሁኔታ ታቃራኒ ትርጉም የሚሰጥ ካልሆነ በስተቀር በህይወት ያለው አባት ወይም እናት ወይም ፍርድ ቤት ለልጁ የሚሾመው ሞግዚት ወይም አሳዳሪ ሁለቱንም ሥልጣን እንደያዘ ይቆጠራል።

አንቀጽ ፪፻፵፮ <u>ለአባትና እናት የተሰጠው መብት</u>

አባትና ወይም እናት ጉዳዩ ጠቃሚ መስሎ የታያቸው እንደሆነ የልጃቸውን የአሳዳሪነት ሥልጣን ራሳቸው ይዘው ሞግዚት ለመሾም ይችላሉ።

አንቀጽ ፪፻፵፯. <u>ለፍርድ ቤት የተሰጠ ሥልጣን</u>

ፍርድ ቤት የልጁን አሳዳሪነት ሞግዚት የመሾም ሥልጣን በያዘበት ጊዜና ይህን ለማድረግ አሳማኝ ምክንያት ሲኖር ከአሳዳሪው በተጨማሪ ሌላ ሞግዚት ለመሾም ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፵፰ <u>ምትክ ሞግዚት -በሞግዚቱና አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ መካከል ስለሚነሳ የጥቅም ግጭት</u>

፩. በሞግዚቱና አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ መካከል የጥቅም ግጭት የተነሣ እንደሆነ ፍርድ ቤት አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ ምትክ ሞግዚት ይሾምለታል።

፪. ምትክ ሞግዚት የሚመረጠው በሞግዚቱ ወይም ወደላይ ከሚቆጠሩ የልጁ ወላጆች ወይም አካለ መጠን ከደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ በአንዳቸው ጥያቄ አቅራቢነት ነው።

አንቀጽ ፪፻#፱ አካለ መጠን ባልደረሱት ብዙ ልጆች መካከል ስለሚነሣ የጥቅም ግጭት

፩. አካለ መጠን ባልደረሱ በብዙ ልጆች መካከል የጥቅም ግጭት የተፈጠረ እንደሆነና የዝህም ተጠሪ ወኪል አንድ የጋራ ሞግዚት ብቻ በሆነ ጊዜ ከዚህ በላይ በአንቀጽ፪፻፰ 8 የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል::

፪. የጥቅም ግጭት የሚፈታወም በሞግዚቱና በምትክ ሞግዚቱመካከል በሚደረግ ስምምነት መሰረት ይሆናል ።

አንቀጽ ፪፻፲ የሥራ አጀማመር

፩. የአሳዳሪነቱ ወይም የሞግዚትነቱ ሥራ የሚጀመረው አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ በሕጉ መሰረት ወይም በፍርድ ውሳኔተመርጠው እንደተሾሙ ወዲያወኑ ነው።

፪. ሆኖም የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ የተሰጠው መሆኑን ከማወቁ በፊት አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ይህን ሥራ ሳይጀምር ለደረሰው ጉዳት ሁሉ በኃላፊነት ሊጠይቅ አይችልም።

አንቀጽ ፪፻፲፩ ሥራው የሚዬታ ስለመሆኑ

የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ እንዲያከናውን ተመርጦ የተሾመ ማንኛውም ሰው ሥራውን የማከናውን ግዴታ አለበት።

አንቀጽ ፪፻፲፪ ሥራው እንዲቀርለት የሚቀርብ ጥያቄ

፩. አንድ ሰው የአሳዳሪነት ወይም ሞግዚትነት ተግባርን ማከናወን በራሱ ላይ ከበድ ያሉ ችግሮችን በአጠቃላይ ኑሮውም ላይ እንቅፋት የሚያስከትልበት ከሆነ ሥራው እንዲቀርለት ፍርድ ቤቱን ሊጠይቅ ይችላል።

፪. እንዲሁም በተጨማሪ ሁኔታ አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ከተሰጠው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራው እንዲሻር ጥያቄ ማቅረብ ይቻላል።

አንቀጽ ፪፻፲፫ በህግ አግባብ የሚሰጥ ልዩ አስተያየት

በዚህ ህግ መሰረት ለአሳዳሪነት ወይም ለሞግዚትነት ስለሚመረጡ ሰዎች የተደነገገው ቢኖርም ከዚህ የሚከተሉት ሰዎች በአሳዳሪነት ወይም በሞግዚትነት እንዳይሾሙ ወይም እንዲሻሩ ጥያቄ ካቀረቡና ይህ ጥያቄ የራሳቸውን ልጆች የሚመለከት ካልሆነ በቀር የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ እንዲሰሩ አይገደዱም፦

ሀ) ዕድሜው ስድሣ አምስት ዓመት የሞላው ሰው፣

ለ) አካለ መጠን ያልደረሱ አራት ልጆች ያሉት ሰው፣

ሐ) በውትድርና የተሰማሩ ሰዎች ።

አንቀጽ ፪፻፺፬ ለጊዜው ሥራውን የማከናወን ግዴታ

፩. የልጁ አሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ ችግር ያደርስብኛል ብሎ ምክንያት በማቅረብ ይህ ኃላፊነት እንዲወገድለት የሚጠይቅ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት በዚህ ሥራ ሌላ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ተተክቶ ሥልጣኑን እስኪረከበው ድረስ የተሰጠውን ሥራ ለጊዜው የማከናወን ግዴታ አለበት።

፪. እንዲሁም በሹመቱ ላይ ተቃውሞ የተነሣበት አሳዳሪ ወይም ሞግዚትም ተመሳሳይ ግዴታ ይኖርበታል።

አንቀጽ ፪፻፺፭ <u>ስለ ሥራው መቅረት</u>

፩. የአሳዳሪው ወይም የሞግዚቱ ሥራ ቀሪ የሚሆነው የሚጠበቀው ልጅ የሞተ እንደሆነ ወይም አካለ መጠን በደረሰ ጊዜ ወይም ከሞግዚት አስተዳደርነፃ በወጣ ጊዜ ነው።

፪. እንዲሁም አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ሲሞት ወይም ችሎታ ሲያጣ ወይም ብቁ ያለመሆኑ ሲገለጽ ወይም ከሥራው ሲሻር ቀሪ ይሆናል።

፫. በመጨረሻም አዲስ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ ሲሾምለት የቀድሞዎቹ ተሿሚዎች ኃላፊነት ያበቃል።

አንቀጽ ፪፻፺፮ <u>ችሎት ማጣት /ሽ/ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ</u>

የራሱን ልጆች በሚመለከት ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር አካል መጠን ያልደረሰ ልጅ የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራን ለማካሄድ ችሎታው የለውም።

አንቀጽ ፪፻፺፯ <u>በፍርድ የተከለከሉ ሰዎች</u>

፩. በፍርድ የተከለከለ ማንኛውም ሰው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራን ለማከናወን አይችልም።

፪. ይህን ሥራ ያከናውን የነበረው አንድ ሰው ችሎታ ያጣ መሆኑ በፍርድ ቤት ውሳኔ የተገለጸ እንደሆነ፣ የዚህ ሰው ሞግዚት በሕግ መሰረት የተከለከለውን ሰው ስራ ተረክቦ በምትክነት ማካሄድ ለሚገባው ሰው ወዲያውኑ ማስታወቅ አለበት።

፫. እንዲህ ያለ ሰው የሌለም እንደሆነ በፍርድ የተከለከለው ሰው ምትክ እንዲደረግለት ሞግዚቱ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ አለበት።

አንቀጽ ፪፻፶፭ <u>ብቁ ስላለመሆን</u>

፩. አንድ ሰው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ ለማካሄድ ብቁ አይደለም ብሎ ፍርድ ቤት ለመወሰን የሚችለው የወንጀል ተግባር በመፈጸሙ የግል ነፃነትን የሚከለክል የእሥራት ወይም የሞት ቅጣት የተፈረደበት ሲሆን ነው።

፪. ፍርድ ቤት የዚህን ዓይነት ቅጣት በአንድ ሰው ላይ በሚወሰንበት ጊዜ ነገሩ ተገቢ መሆኑን የገመተ እንደሆነ የተፈረደበት ሰው ለዚህ ሥራ ብቁ አለመሆኑ ጭምር ለመወሰን ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፶፮ <u>የአሳዳሪው መሻር</u>

፩. አካለ መጠን ላልደረሰ ልጅ አሳዳሪ እንዲሆን የተሾመ ሰው ልጅ ለኑሮው አስፈላጊ የሆነውን ጥበቃ ላያገኝ ወይም ከሞራል ጋር የሚስማማ የአእምሮ አስተዳደግ ወይም ከችሎታው ጋር ተመዛዛኝ የሆነ ትምህርት እንዲያገኝ ሳይደረግለት የቀረ እንደሆነ አሳዳሪው እንዲሻር ፍርድ ቤት ሊወስን ይችላል።

፪. ይህንንም ውሳኔ ለመስጠት አሳዳሪው የሚኖርበትን የአካባቢ ሁኔታ ጊዜውንም መመርመርና መሰረት ማድረግ አስፈላጊ ነው።

፫. በተለይም ፍርድ ቤቱ አሳዳሪውን ለመሻር የሚችለውን አካል መጠን ያልደረሰው ልጅ ወንጀል መሥራቱ የተረጋገጠ ሲሆንና ይህንንም ወንጀል የፈጸመው በመጥፎ አስተዳደግ ወይም በአሳዳሪው ጉድለት ተገቢውን የግብረ ገብ ትምህረት ለማግኘት ባለመቻሉ የሆነ እንደሆነ ነው።

አንቀጽ ፪፻፶፯ <u>የሞግዚቱ መሻር</u>

አካለ መጠን ላልደረሰ ልጅ ሞግዚት የሆነ ሰው እንዲሻር ፍርድ ቤት የሚወስነው ሞግዚቱ የልጁን ንብረትና ሀብት በመጥፎ ሁኔታ ያስተዳደረና አጠባበቁም በቂ ያልሆነ እንደሆነ ወይም ልጁን በሞግዚትነት እንዲያስተዳድር ሥልጣን የሰጠው ሰው ወይም አካል የሰጠውን መመሪያና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት ሳይጠበቅና ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ ወይም ዕዳ ለመክፈል ያለመቻሉ በፍርድ ውሳኔ የተረጋገጠ እንደሆነ ነው።

አንቀጽ ፪፻፶፰ <u>የወላጆች መሻር</u>

፩. የልጁ አባት ወይም እናት ወይም ሌሎች ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆቹ ከልጃቸው አሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራቸው እንዲሻሩ መወሰን ሲያስፈልግ ፍርድ ቤቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅበታል።

፪. ፍርድ ቤቱ በዚህ ጉዳይ ላይ የሰጠውን ውሳኔ በተሻረው ወገን ጠያቂነት በማንናውም ጊዜ እንደገና ሊመረምር ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፶**2** ሥነ ሥርዓት

1 አሳዳሪ ውይም ሞግዚት እንዲሻር የሚቀርበው ጥያቄ በማናቸውም በጉዳዩ ያገባኛል ባይ ወገን ወይም በዐቃቤ ህግ በኩል ሊቀርብ ይችላል።

2 ፍርድ ቤቱ አሳዳሪውን ወይም ሞግዚቱን ለመሻር ከመወሰኑ በፊት በእርሱ በኩል ያለውን ሀሳብ ሊያዳምጠው ይገባል።

፫. ሆኖም ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ የተመለከተውን ሲያከናውን በልጁ ደህንነት ወይም ሀብት ላይ ተጨማሪ ጉዳት ይደርሳል ተብሎ የሚገመት ከሆነ ተገቢ መስሎ የታየውን ዝዘዘያዊ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

አንቀጽ ፪፪፰ **3** <u>የፍርድ ቤት ኃላፊነት</u>

፩. ፍርድ ቤት አንድን ሰው አካለ መጠን ላልደረሰ ልጅ አሳዳሪነት ወይም ሞግዚትነት ለመሾምሲመርጥ ወይም የተሾመውን ከሥራው ሲሽር ከውሳኔው በፊት በተቻለ መጠን ከልጁ ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች አካል መጠን ከደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ ጋር መመካከር ይገባል።

፪. አስፈላጊ መስሎ ሲታየው አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ያለውን ሃሣብ ሊያዳምጥ ይችላል።

፫. ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን ሊሰጥ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ጥቅም የማይጓድልበትን አሰራር ብቻ መከተል እንጂ የቀረቡለትን ሃሳቦች የመቀበል ግዴታ አይኖርበትም።

አንቀጽ ፪፪፱ **4** <u>ሥራው ያለዋጋ የሚከናወን ስለመሆኑ</u>

፩. አሳዳሪነትና የሞግዚትነት ሥራ የሚከናወነው ማናቸውም ዋጋ ሳይከፈልበት በነፃ ነው።

፪. ሆኖም አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ሥራውን ለማከናወን ረጅም ጊዜ የሚጠየቀው የሆነ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ አንድ የተወሰነ አበል ሊቆረጥለት ይችላል።

፫. ይህም አበል አካለ መጠን ካልደረሰው ልጅ የሃብት ገቢ ላይ ካልሆነ በስተቀር ከሌላ ሃብት ሊወሰድ አይችልም። የአበሉም ልክ ከጠቅላላ ሃብት ገቢ ሲሶ ሊበልጥ አይችልም።

አንቀጽ ፪፪፲ **5** <u>የሥራው አካሄድ የግል ስለመሆኑ</u>

፩. የአሳዳሪነቱ ወይም የሞግዚትነቱ ሥራ የግል ጠባይ የያዘ ስለሆነ ሥራውን የሚያከናውነው ራሱ እንጂ ለአሳዳሪው ወይም ለሞግዚቱ ወራሾች ሊተላለፍ አይችልም።

፪. ወራሾቹ በሃላፊነት የሚጠየቁት አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ በፈፀመው የሥራ አካሄድ ጉድለት ብቻ ነው። ይኸውም በውርስ ህግ መሰረት ይወሰናል።

አንቀጽ ፪፪፲ **6** <u>የወራሾች ግዴታ</u>

፩. የአንድ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ወራሾች አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ እንደሞተ ወዲያውኑ በዚህ ህግ አንቀጽ ፭፪"9 በተመለከተው መሰረት ለሚቹ ምትክ ሊሆን ለሚገባው ሰው የማስታወቅ ግዴታ አለባቸው።

፪. የዚህ አይነት ሰው የሌለ እንደሆነ በሚቹ ምትክ የሚመረጠው ሰው እንዲሾም ለፍርድ ቤት ማስታወቅ አለባቸው።

፫. የአሳዳሪው ወይም የሞግዚቱ ወራሾች ከዚህ በላይ ባሉት ንዑሳን አንቀጾች የተመለከቱትን ግዴታዎችን እስኪወጡ ድረስ አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅም ሆነ ለሌላ ሦስተኛ ወገኖች ኃላፊዎች ሆነው ይቀያሉ።

አንቀጽ ፪፪፭ **7** የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ማስረጃ

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አሳዳሪነቱን ወይም ሞግዚትነቱን የሚያስረዳለት ጽሑፍ እንዲሰጠው አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ፍርድ ቤቱን ለመጠየቅ ይችላል

አንቀጽ ፪፪፭ **8** ከሞግዚት የሚመሳሰል ሁኔታ

ሞግዚትን የሚመለከታት የዚህ ህግ ድንጋጌዎች በምትክ ሞግዚት ጉዳይም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

ክፍል ፫

የአሳዳሪና የሞግዚቱ ሥልጣን

ንዑስ ክፍል ፩

አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ አስተዳደግና ጥበቃ

አንቀጽ ፪፪**%9** አሳዳሪው የመንግስት ተቋማትን እገዛ መጠየቅ ስለመቻሉ

አሳዳሪው ከዚህ በታች በተመለከቱ አንቀጾች የተሰጠውን ሥልጣን በሥራ ላይ ለማዋል እንዲችል አግባብነት ያላቸውን የመንግስት ተቋሞች እገዛ ሊጠይቅ ይችላል።

አንቀጽ ፪፪፫. አካለ መጠን ስላልደረሰ ልጅ መኖሪያ ቦታ

1 አሳዳሪው አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ የመኖሪያ ቦታ ይወስናል።

2 አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ያለአሳዳሪው ፈቃድ የተመደበለትን የመኖሪያ ቦታ ሊተው አይችልም።

3 አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ የተመደበለትን የመኖሪያ ቦታ ትቶ የሄደ እንደሆነ አሳዳሪው ወደ መኖሪያው ቦታ እንዲመለስ ሊያስገድደው ይችላል።

አንቀጽ ፪፪፫ **1.**አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ጤና አጠባበቅ

1 አሳዳሪው አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ጤንነት ሁኔታ ይከታተላል።

2 አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ሲታመም ከህመሙ እንዲፈወስ አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳል።

አንቀጽ ፪፻፫ **2.** አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ አስተዳደግ

፩ አሳዳሪው አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ አስተዳደግ ይመራል።

፪ አሳዳሪው አካለ መጠንላልደረሰው ልጅ መልካም አስተዳደግ ተገቢነት ያለው የዲሲፒሊን እርምጃ ለመውሰድ ይችላል።

አንቀፅ ፪፻፬ **3** <u>አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ማህበራዊ ግኙኝነት</u>

፩ አሳዳሪው አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ማህበራዊ ግንኙነት ይመራል፤ይቆጣጠራል።

፪ ሆኖም አሳዳጊው በቂ ምክንያት ሳይኖረው አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ወደ ላይ ከሚቆጠሩ

ወላጆቹ ጋር ግንኙነት እንዳያደርግ ሊያግደው አይችልም።

አንቀፅ ፪፻፭ **4** <u>አጠቃላይ እና የሙያ ትምህርት የመስጠት ግዴታ</u>

አሳዳሪው አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ ዕድሜና ችሎታ ተመጣጣኝ የሆነ አጠቃላይ ትምህርት ወይም የሙያ ስልጠና እንዲያገኝ ማድረግ አለበት።

አንቀፅ ፪፻፮ **5** <u>አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ገቢ /፩/ መሰረቱ</u>

፩ አሳዳሪው አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ገቢዎች በመቀበል ለልጅዬው ጥቅም ያውላል።

፪ አሳሪው ገንዘቡን ለምን አገልግሎት እንዳዋለው መግለጫ ለመስጠት አይገደድም።

አንቀፅ ፪፻፯ **6** .<u>ከፍተኛ ስለሆነ ገቢ</u>

፩. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ገቢ ከፍተኛ ሲሆንና አሳዳሪው የልጁ አባት ወይም እናት ያልሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤት ከዚህ በላይ ፪፻፭ **5** /፪/ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚ እንዳይሆን ሊያግድ ይችላል።

፪. ፍርድ ቤቱ ትዕዛዙን በሚሰጥበት ጊዜ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ላስተዳደጉና ትምህርቱ በቂ ነው የሚለውን የገንዘብ መጠንና የሚከፈልበትን ጊዜ በመወሰን ለአሳዳሪው እንዲሰጠው ይደረጋል።

፫. ተራፊውን ገንዘብ በአትራፊ ስራ ላይ እንዲያውለው በሞግዚቱ እጅ ተቀማጭ ይደረጋል።

አንቀፅ ፪፻፰ **7** <u>አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ከስራው ስለሚያገኘው ገቢ</u>

፩ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ዕድሜው ከ፲፬ ዓመት በላይ ሲሆን ከስራው የሚያገኘውን ገቢ እራሱ ይቀበላል።

፪ ለራሱ ቀለብ የሚሆነውን ለአሳዳሪው ከሰጠ በኃላ ቀሪውን ገንዘብ በዚህ ህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሊጠቀምበት ሙሉ ነፃነት አለው።

አንቀፅ ፪፻፸፰ <u>በስጦታ ወይም በውርስ ስለተላለፉ ሀብቶች</u>

፩. አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ በስጦታ ወይም በውርስ ሀብት የሚያስተላልፍ ሰው ልጁ አካለ መጠን ሳይደርስ አሳዳሪው ተቀብሎ ጥቅም ላይ እንዳያውለው ሊያዝ ይችላል።

፪. በስጦታ ውል ወይም በኑዛዜው ስለ ንብረቱ አስተዳደርና ስለሚገኘውም ገቢ የተመለከቱት ሀይለ ቃሎች ተፈፃሚ መሆን አለባቸው።

አንቀፅ ፪፻፸፱. <u>የመክፈያ ጊዜያቸው ያልደረሱ ገቢዎች</u>

የመክፈያ ጊዜያቸውን ያልደረሱ ገቢዎችን አሳዳሪው ግዴታ ሊገባባቸው አይችልም።

አንቀፅ ፪፻፹. <u>ስለ ወላጆች ስልጣን</u>

፩ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ አባትና እናት በጋራ አሳዳሪዎቹ በሆኑ ጊዜ የአሳዳሪነት ተግባራቸውን በመመካከርና በመግባባት ይወጣሉ።

፪ አባትና እናት ያለመግባባታቸውን በግላቸው ወይም በሽምግልና ለመፍታት ያልቻሉ እንደሆነ፤ ከሁለቱ አንደኛው በሚያቀርበው አቤቱታ መነሻነት ፍርድ ቤቱ አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ ጥቅም ቅድሚያ በመስጠት ውሳኔ ይሰጣል።

፫ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ /፪/ የተመለከተው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ አባትና እናት በአሳዳሪነታቸው በሚሰጡት ውሳኔ ላይ አቤቱታ ሊቀርብበት አይችልም።

አንቀፅ ፪፻፹፩ <u>የወላጆች መለያየት</u>

ወላጆች በመለያየታቸው ምክንያት የአሳዳሪነቱ ስልጣን የአንደኛው ወላጅ ብቻ የሆነ እንደሆነ፤ይኸው ወላጅ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የአሳዳሪነት ተግባር በማከናወን ላይ የሌለው ወገን ወደ ላይ ከሚቆጠሩ ወላጆች ወይም አካለ መጠን ከደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ አንዳቸው አቤቱታ ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ።

አንቀፅ ፪፻፹፪ <u>አሳዳሪው አካል መጠን ያልደረሰው ልጅ ወላጅ በማይሆንበት ጊዜ</u>

አሳዳሪው አካል መጠን ያልደረሰው ልጅ ወላጅ ያልሆነ እንደሆነ፤በልጁ አስተዳደግ ረገድ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ከወላጆቹ አንዳቸው አንዳቸው ወይም ሌላ በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ሰው ወይም ዐቃቤ ህግ ለፍርድ ቤት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል።

ንዑስ ክፍል ፪

አካለ መጠን ያልደረሰን ልጅ ንብረት ስለማስተዳደር

አንቀጽ ፪፻፹፫መሠረቱ

፩. ሀብቱንና ንብረት ነክ ጥቅሞቹን በተመለከተ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ በሞግዚቱ ይወከላል።

፪. ሀብቱንና ንብረት ነክ ጥቅሞቹን በማስተዳደር ረገድ ሞግዚቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ የማድረግ ግዴታ አለበት።

አንቀጽ ፪፻፹፬የንብረት ቆጠራው የዋጋ ግምት /፩/ ሞግዚቱ የሞግዚትነት ስራውን ከጀመረ በኋላ

፩. ሞግዚቱ፣የሞግዚትነቱን ስራ ከጀመረ በኋላ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ሶስት ምስክሮች ባሉበት አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ይቆጣጠራል፤የዋጋውንም ግምት ያወጣል።

፪. ሞግዚቱ አካለ መጠን ካልደረሰው ልጅ የሚጠይቀው ዕዳ ሲኖር፣በንብረት ቆጠራው መዝገብ በወቅቱ ካላሰፈረው በስተቀር የዕዳው ክፍያ ቀሪ ይሆንበታል።

አንቀጽ ፪፻፹፭/፪/ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ የውርስ ሀብት

፩. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወራሽ በሚሆንበት ጊዜ ሞግዚቱ ስለልጁ ሆነ ውርሱን ከመቀበሉ አስቀድሞ ሶስት ምስክሮች ባሉበት የውርስ ንብረቱን ቆጠራ ያከናውናል፤ የዋጋውን ግምት ያወጣል።

፪. ሞግዚቱ ከውርስ ሀብቱ ውስጥ ድርሻ ያለው እንደሆነ፣ ይህንኑ በንብረት ቆጠራው መዝገብ ያላሰፈረው እንደሆነ ድርሻው ቀሪ ይሆንበታል።

፫. የንብረት ቆጠራው ባለመከናወኑ ወይም በአግባቡ ባለመሰራቱ በሚደርስ ጉዳት ሞግዚቱ በኃላፊነት ይጠየቅበታል።

አንቀጽ ፪፻፹፮ የሞግዚቱ ንብረት አካለ መጠን ካልደረሰው ልጅ ንብረት ጋር ስለሚቀላቀልበት ሁኔታ

፩. ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ከግል ንብረቱ ጋር እንዳይቀላቀል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ ማድረግ አለበት።

፪. በተለይም አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ገንዘብ ሞግዚቱ በራሱ የባንክ ሂሳብ ማስቀመጥ ወይም እንዲቀመጥ ማድረግ አይፈቀድለትም።

አንቀጽ ፪፻፹፯ የገንዘብ ሰነዶችና ሌሎች ውድ ዕቃዎች ስለሚቀመጡበት ሁኔታ

አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት በማስተዳደር ረገድ ችግር የሚፈጥር ካልሆነ በስተቀር፣የገንዘብ ሰነዶችን፣ውድ ዕቃዎችን፣ጠቃሚ ጽሁፎችንና ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮችን ሁሉ ሞግዚቱ ሊጠፋ ወይም ሊባክኑ በማይችሉበት አስተማማኝ ስፍራ ማስቀመጥ አለበት።

አንቀጽ ፪፻፹፭ <u>የፍርድ ቤት ስልጣን</u>

፩.አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ሞግዚት የልጁ ወላጅ ባልሆነ ጊዜ፣አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ሀብት መልካም አስተዳደር በሚመለከት ለሞግዚቱ *መመሪያ* እንዲሰጥ የልጁ ወደላይ በሚቆጠሩ ወላጆችወይም አካለ መጠን ከደረሱ ወንድሞቹ ወይም እህቶቹ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ።

፪. ፍርድ ቤቱ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ሀብት አጠቃላይ ሁኔታ፣የሞግዚቱን ችሎታና የልጅየውን ጥቅም በማመዛዘን ስለሀብቱ አስተዳደር ጠቃሚ መስሎ የሚታየውን *መመሪያ* ይሰጠዋል።

አንቀጽ ፪፻፹፮ <u>አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ በስጦታ ወይም በውርስ ስለሚተላለፍ ንብረት</u>

፩. አካለመጠን ላልደረሰ ልጅ ንብረት በስጦታ ወይም በውርስ የሚያስተላልፍ ሰው የንብረቱን አስተዳደር በሚመለከት ተገቢ ናቸው የሚላቸውን የአሰራር *መመሪያዎችን* ሞግዚቱ እንዲከተል ሊያዝ ይችላል።

፪. የአሰራር *መመሪያዎችን* ተከትሎ የማይቻል ወይም አካመጠን ባልደረሰ ልጅ ጥቅም ላይ ጉዳት የሚደርስበት *መስሎ* የታየው እንደሆነ፣ሞግዚት *መመሪያዎቹ* እንዲስተካከሉለት ፍርድ ቤት ሊጠይቅ ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፹፯ ስለ ንግድ ድርጅቶችና ሌሎች መሰል ድርጅቶች

፩. የንግድ፣ የኢንዱስትሪ ወይም ሌሎች መሰል ድርጅቶች አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ሀብት አካል የሆኑ እንደሆኑ፣ወደላይ ከሚቆጠሩ ወላጆቹ ወይም አካለ መጠን ከደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ አንዳቸው በሚያቀርቡት ጥያቄ የልጁ አባት ወይም እናት ያልሆነው ሞግዚት ንብረቱን እንዲያጣራ ወይም እንዳለ እንዲቀጥል እንዲያደርግ ፍርድ ቤቱ ሊያዘው ይችላል።

፪. ፍርድ ቤቱ ይህንን ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ሞግዚትነቱን ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ የሞግዚቱን ችሎታና አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ጥቅም ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

አንቀጽ ፪፻፹፰ <u>አንዳንድ ንብረቶች ስለመሸጥ</u>

፩. ሞግዚቱ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት የሆኑ የሚንቀሳቀሱ ግዙፍ ንብረቶችን፣አክሲዮኖችንና የገንዘብ ሰነዶችን ለመሸጥ ይችላል።

፪. በልጁ አባት ወይም እናት ላይ ካልሆነ በስተቀር፣በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ማናቸውም ሰው ጥያቄ ሲያቀርብለት ፍርድ ቤት ስለሽያጩ መመሪያ ለመስጠት ወይም ሽያጩ እንዳይካሄድ ለመከልከል ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፯፪ <u>ለአምጭው እንዲከፈል ስለሚሉ ሰነዶች</u>

፩. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ አባት ወይም እናት ያልሆነ ሞግዚት ለአምጭው እንዲከፈል የሚሉ ሰነዶች የልጁ ሀብት ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ በሶስት ወራት ውስጥ እንዲሸጡ ወይም በልጁ ስም በተመዘገቡ ሰነዶች እንዲለወጡ ማድረግ አለበት።

፪. ሞግዚቱ ጥያቄ ሲያቀርብለት፣ ፍርድ ቤቱ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /፩/ ከተመለከተው ግዴታ ነፃ እንዲሆን ሊያዝ ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፯፫ ዕዳዎችና ገቢ ገንዘቦች

፩. ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ዕዳዎች ከልጁ ሀብት በመቀነስ ይከፍላል።

፪. አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ መከፈል የሚገባውን ካፒታልና ሌላ ገቢ ይቀበልለታል፤ስለመቀበሉ ለማረጋገጥም ደረሰኝ ይሰጠዋል።

አንቀጽ ፪፻፯፬ ካፒታል አትራፊ በሆነ ስራ ላይ ስለማዋል/፩/ የሞግዚቱ ግዴታ

፩. የገንዘቡ መጠን ከ፭፻ ብር በላይ የሆነ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ካፒታል ሞግዚቱ አትራፊ በሆነ ስራ ላይ ማዋል አለበት።

፪. ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/፩/ የተመለከተውን የገንዘብ መጠን ሊያሻሽለው ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፯፭ የጊዜ ገደብ

፩. ካፒታሉ በሞግዚቱ እጅ በገባ በሶስት ወራት ውስጥ በአትራፊ ስራ ላይ ማዋል አለበት።

፪. ፍርድ ቤቱ የጊዜውን መጠን ሊያሻሽለው ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፯፮ ኃላፊነት

፩. በአትራፊ ስራ ላልዋለው ገንዘብ ሞግዚቱ ህጋዊ ወለዱን አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ መክፈል አለበት።

፪. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ተጨማሪ የጉዳት ካሳ እንዲከፍል ሊፈረድበት ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፯፯ ገቢዎች

፩. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ገቢዎች፣ገቢዎቹ በቂ ሆነው የማይገኙ ሲሆንም ከሀብቱ ቀንሶ ለአስተዳደጉና ለትምህርቱ አገልግሎት እንዲውል ሞግዚቱ ለአሳዳሪው ይሰጠዋል።

፪. ፍርድ ቤቱ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በስተቀር፣ለዚሁ አገልግሎት የሚውለው ገንዘብ በየወሩ ለአሳዳሪው ይከፍላል።

፫. የአከፋፈል ሁኔታው በአሳዳሪውና በሞግዚቱ ስምምነት ወይም በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሳኔ መሰረት ሊሻሻል ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፯ **8** የኪራይ ውሎች

በፍርድ ቤትፈቃድ የተደረጉ ካልሆኑ በስተቀር፣ሞግዚቱ የሚያደርጋቸውን የኪራይ ውሎች ልጅየው አካለመጠን ከደረሰ ከሶስት አመታት በኋላ እንዲፈጽማቸው አይገደድም።

አንቀጽ፪፻፯ **9** ስለውርስ

፩. ልጁ በውርስ የሚያገኘውን ንብረት ሞግዚቱ ይቀበላል።

፪. ሞግዚቱ የውርስ ሀብት ዕዳውን ለመክፈል ፈጽሞ የማይችል ካልሆነ በስተቀር ውርሱን አልፈልግም ለማለት አይችልም።

አንቀጽ ፫፻ ስለሥጦታ

፩. አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ የሚሰጠው ስጦታ ጠቃሚነት የለውም በማለት ካልሆነ በቀር ሞግዚቱ አልቀበልም ለማለት አይችልም።

፪. በተለምዶ ከሚሰጡ አነስተኛ ስጦታዎች ውጭ ሞግዚቱ አካለመጠንያልደረሰውን ልጅ ንብረት በልጁ ስም በስጦታ መስጠት አይችልም።

አንቀጽ ፫፻፩ የዋስትና ግዴታ መግባት የማይችል ስለመሆኑ

ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ለሌላ ሰው ዕዳ በዋስትናሊያሲይዝ አይችልም።

አንቀጽ ፫፻፪ ስለግልግል

ከርክር የሚደረግበት ጥቅም ከአንድ ሺህ ብር ያነሰ ካልሆነ ወይም አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ጥቅም በሚመለከት ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሞግዚቱ ጉዳዩን በግልግል ለመጨረስ አይችልም።

አንቀጽ ፫፻፫ <u>ሞግዚቱ አካለ መጠን ካልደረሰው ልጅ ጋር ስለሚያደርጋቸው ውሎች</u>

፩. ሞግዚቱ ፍ/ቤት ካልተፈቀደለት በስተቀር አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ለመግዛት፣ በኪራይ ለመጠቀም ወይም ሌላ ማናቸውንም ውል ከእርሱ ጋር ለመፈፀም አይችልም።

፪. እንዲሁም ሞግዚቱ በፍ/ቤት ካልተፈቀደለት በስተቀር አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ላይ

ማናቸውም መብት ወይም ገንዘብ የሚጠይቅበትን መብት ለመቀበል አይችልም።

አንቀጽ ፫፻፱ ስለብድር

ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሞግዚቱ አካለመጠን ባደረሰው ልጅ ስም የብድር ውል ለመዋዋል አይችልም።

አንቀጽ ፫፻፲ አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ጋር መመካከር ስለማስፈልጉ

፩. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ዕድሜ ከአስራ አራት ዓመት ያነሰ ካልሆነ በስተቀርሞግዚቱ የልጁ ዕድሜ በሚፈቅድለት መጠንና እርሱን የሚመለከቱ ከፍተኛ ጉዳዮች በተነሱ ጊዜ አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ማማከር አለበት።

፪. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ፈቃዱን መስጠቱ ሞግዚቱን ከተጠያቂነት አያድነውም።

አንቀጽ ፫፻፲ ሞግዚቱ አካለመጠን ያለደረሰው ልጅ እንዲሰራ ስለሚሰጠው ፈቃድ/ፍ/

፩. አከለመጠን ያልደረሰው ልጅ ዕድሜና የገንዘብ አቅም መሰረት በማድረግ የዕለትጉዳዮችንየሚመለከቱ ውሎችን ብቻ እንዲያደርግ ሞግዚቱ ፈቃድ ሊሰጠውይችላል።

፪. ይኸው ፈቃድ በዝምታ ሊሰጥ ይችላል።

አንቀጽ ፫፻፲ የዕለት ጉዳዮች

፩. ድርጊቱ እንዲፈፀም የፍርድ ቤት ፈቃድ የሚያስፈልገው እንደሆነ በምንም መንገድ የዕለትጉዳይ ሊባል አይችልም።

፪. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ከሶስት መቶ ብር በላይ ግዴታ እንዲገባ የሚያስገድደው ሲሆን ድርጊቱ የዕለት ጉዳይ ነው ሊባል አይችልም።

አንቀጽ ፫፻፲ በሞግዚቱ ላይ ስለሚኖረው ውጤት

አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ በሞግዚት ፈቃድ ለሚገባቸው ግዴታዎችሞግዚቱ ለሶስተኛ ወገኖች ዋስ ነው።

አንቀጽ ፫፻፲ ኑዛዜ

፩. ሞግዚቱ አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ስም ኑዛዜ ሊያደርግ አይችልም።

፪. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ፲፯ ዓመት ሳይላሞው ኑዛዜ ማድረግ አይችልም።

፫. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ፲፯ ዓመት ሳይሞላው የሚያደርገው ኑዛዜ ፲፯ዓመት ከሞላውበኃላ ባይሰርዘውም ውጤት አይኖረውም።

አንቀጽ ፫፻፲. <u>ንብረት ለማስተዳደር ሞግዚት ስለሚያደርገው ወጪ</u>

ሞግዚቱ አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ ጥቅም ሲባል ከግሉ የሚያወጣቸውወጪዎች እንዲተኩለት መብት አለው።

አንቀጽ ፫፻፲፩. <u>አካለመጠን ስላልደረሰው ልጅ ሀብት አስተዳደር ሪፖርት ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ</u>

፩. ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ሀብት አስተዳደር ሁኔታና ሂሳቡን የሚያመለክት ሪፖርት አዘጋጅቶ መያዝ አለበት።

፪. አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ወይም አካለመጠን የደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ በጋራ ወይም በተናጠል ጥያቄ ሲያቀርቡለት ሞግዚቱ የአስተዳደርና የሂሳብ ሪፖርቱን እንዲመለከቱት ያደርጋል።

አንቀጽ ፫፻፲፪ . <u>ተፈጻሚነት</u>

በዚህ ህግ አንቀጽ ፪፻፫ 8 እስከ ፪፻፵ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ለሞግዚትምተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

<u>ክፍል ፬</u>

<u>አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ ለመጠበቅ የተመለከቱትን ደንቦች መጣስ ስለሚያስከትለው ዉጤት</u>

<u>ንዑስ ክፍል ፩</u>

<u>አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ሥራዎች</u>

አንቀጽ ፫፻፲፫. <u>መሰረቱ</u>

አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ከሥልጣኑ በላይ የሚፈጽማቸው ድርጊቶች ሁሉፈራሽ ይሆናሉ።

አንቀጽ ፫፻፲፬.<u>እንዲፈርስ ስለመጠየቅ</u>

አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ የፈጸማቸው ህጋዊ ድርጊቶች እንዲፈርሱ መጠየቅ የሚችሉት አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ወይም ወራሾች ወይም ወኪሎችናቸው።

አንቀጽ ፫፻፲፭. ስለተዋዋዮች ቅን ልቦና

፩. ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፫፻፲ 3 የተደነገገው ቢኖርም ሌላው ተዋዋይ ወገን ከልጁጋር የተዋዋለው ይህንን እንዲያደርግ ፈቃድ አለው ብሎ በቅን ልቦና በማመን የሆነ እንደሆነ ውሉ የፀና ይሆናል።

፪. ሌላው ተዋዋይ በልጁ አላዋቂነት የተጠቀመ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገገው ተፈጻሚነት አይኖረውም።

አንቀጽ ፫፻፲ 6. ስለሚመለስ ገንዘብ

፩. አካለመጠን ላልደረሰዉ ልጅ የተከፋለ ገንዘብ ሊመለስ የሚችለው ውሉ እንዲፈርስ ክስ በቀረበበት ቀን በልጽጎ በተገኘው መጠን ብቻ ይሆናል።

፪. ከዚህ ሁኔታ ውጪ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ለመመለስ አይገደደም።

፫. ሞግዚቱ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ሲል ለፈጸማቸው ህጋዊ ድርጊት ኃላፊ አይሆንም።

አንቀጽ ፫፻፲፰ 7.ከውል ውጪ ስለሚደርስ ኃላፊነትና ያለአግባብ ስለመበልፀግ /፩/ መሰረቱ

አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ህገ ወጥ በሆኑ ሥራዎች ያለአግባብ የበለፀገ ወይም በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ በፍትሐብሔር ህግ ውስጥ ከውል ውጭ ስለሚደርስ ኃላፊነትና ያለአግባብ ስለመበልጸግ በተደነገገው መሰረት ተጠያቂ ይሆናል።

አንቀጽ ፫፻፲፱%. አካለመጠን ሳይደርስ ደርሻለሁ ማለት

፩. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ አካለ መጠን ሳይደርስ ደርሻለሁ ብሎ ቢናገርም እንኳን ይህን በመናገሩ ብቻ አካለመጠን ባለመድረሱ ምክንያት የሚጠቀምበትን መብት አያጣም።

፪. እንዲሁም አካለ መጠን ደርሻለሁ ማለቱ ከውል ውጭ የሆነ ኃላፊነትን የሚያመጣ ጥፋት ሆኖ አይቆጠርበትም።

ንዑስ ክፍል ፪

የሞግዚቱ ህጋዊ ድርጊቶች

አንቀጽ ፫፱ 9. በደንብ ስለተፈፀሙ ድርጊቶች

፩. ሞግዚቱ አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ የፈፀማቸው ህጋዊ ድርጊቶች ሁሉ ልጁ አካለ መጠን በደረሰ ጊዜ እንዲፈጽማቸው ተቆጥረው በኃላፊነት ያስጠይቁታል።

፪. ሞግዚቱ በኃላፊነት እጠየቅበታለሁ ሲል ግዴታ የገባበት ወይም በህግ መሰረት ግዴታ የተጣለበት ካልሆነ በስተቀር አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ሲል ለፈፀማቸው ህጋዊ ደርጊቶች ኃላፊ አይሆንም።

አንቀጽ ፫፪፩. ህጋዊ ድንጋጌዎች ስለመተላለፍ

የህግ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ሞግዚቱ ለሚፈጽማቸው ድርጊቶች ወኪል የሆነ ሰው ከተሰጠው ሥልጣን በላይ በሚሰራበት ጊዜ አግባብነት ያላቸው የውክልና ህግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

አንቀጽ ፫፪፪ 1. ስለ ሦስተኛ ወገኖች

፩. ፍርድ ቤት ለሞግዚቱ የተሰጠውን መመሪያ ሦስተኛ ወገኖች ካላወቁ ወይም ማወቅ የሚገባቸው ካልሆነ በስተቀር ሞግዚቱ መመሪያውን መተላለፉ በሦስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም።

፪. አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ንብረቱን የሰጠ ወይም የተናዘዘ ወይም የተወ ሰው ለሞግዚቱ መመሪያ በሰጠ ጊዜም የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል።

አንቀጽ ፫፪፫ 2. ስለምትክ ሞግዚት

በዚህ ንዑስ ክፍል የተደነገጉ ድንጋጌዎች በምትክ ሞግዚትም ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

ንዑስ ክፍል ፫

በኃላፊነት ሊያስጠይቁ ስለሚችሉ ድርጊቶች

ቮያሽ 3. ስለሞግዚት

፩. ሞግዚቱ በፈፀመው የንብረት አስተዳደር ጉድለት ምክንያት ወይም መመሪያ ባለመከበሩ ወይም የእርሱ ጥቅም አካለ መጠን ካልደረሰ ልጅ ጥቅም ጋር የሚጋጭ ሆኖ እያለ ድርጊቱን በመፈፀሙ አካለመጠን ባልደረሰ ልጅ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ሁሉ በኃላፊነት ይጠየቃል።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው ድንጋጌ በምትክ ሞግዚትም ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

ክፍል ፭

አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ ማጣት ስለመቅረቱ

አንቀጽ ቮያሽ 4. ችሎታ ማጣት ስለሚቀርባቸው ምክንያቶች

አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ የለውም መባሉ የሚቀረው

ሀ/ አካለ መጠን ሲደርስ ወይም

ለ/ ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ ይውጣ ሲባል ነው።

ንዑስ ክፍል ፮

ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ ስለመውጣት

አንቀጽ ቮያሽ 5 . ጋብቻ

አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ በዚህ ህግ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ /፪/ በተመለከተው መሰረት ጋብቻ የፈፀመ እንደሆነ በጋብቻው ምክንያት ብቻ ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ ይወጣል።

አንቀጽ ቮያሽ 6 . በልዩ ሁኔታ ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ ስለመውጣት

፩. አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ፲፱ ዓመት ሲሞላው አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ወይም ያገባኛል የሚል ሌላ ሰው ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ እንዲወጣ መጠየቅ

ይችላል።

፪. ፍርድ ቤት ጥያቄው ሲቀርብለት የልጁን ሁኔታና ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ ነጻ አንዲወጣ የተጠየቀበትን ምክንያት ምክንያት ተመልክቶ ከሞግዚት አስ ተዳደር ነጻ መሆኑ ለልጁ የሚጠቅም ሆኖ ካገኘው ጥያቄውን ተቀብሎ ሊፈቅድ ይችላል።

አንቀጽ ፶፱፭ **7.**<u>ውጤቶች</u>

ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ የወጣ ልጅ በህግ አካለ መጠን እንደደረሰ ሆኖ ይቆጠራል።

አንቀጽ ፫፱፭ **8.**<u>የማይሻር ስለመሆኑ</u>

፩. አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ እንዲሆን የተሰጠ ፈቃድ ሊሻር አይችልም።

፪. በጋብቻ ምክንያት የተገኘው ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ የመሆን ሁኔታ ጋብቻው ቢፈርስም እንኳን ውጤቱ እንደተጠበቀ ይቀራል።

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ የተደነገገው ቢኖርም ጋብቻው የፈረሰው ለጋብቻ የተፈቀደው ህጋዊ እድሜ ባለመጠበቁ ምክንያት የሆነ እንደሆነ ከሞግዚት አስተዳደር መውጣቱን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ የታየውን ሊወስን ይችላል።

ንዑስ ክፍል ፪

<u>ሞግዚትነት ሥራ ሂሳቦችን ስለማስታወቅ</u>

አንቀጽ ፫፱፭ **9.**<u>መሰረቱ</u>

፩. ሞግዚቱ የሞግዚትነት ሥራ ሲያበቃ ሞግዚት ሆኖ ለአስተዳደረው ሰውወይም ለወራሾቹ ያስተዳደረበትን ሂሳብ ማቅረብ አለበት።

፪. እንዲሁም በሞግዚትነት ያስተዳደረውን ሰው ንብረት ሁሉ ማስረከብ የመብቶቹን ሁኔታና የሚገደድባቸው ዕዳዎች ካሉም ማስታቅ አለበት።

አንቀጽ ፫፻፴ **7.**<u>የንብቶች በመዝገብ አለመግባት</u>

፩. ሞግዚቱ የሞግዚትነት ሥራዉን በያዘበት ጊዜ ወይም አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ በውርስ ሀብት ሲሰጠውየንብቶቹን ዝርዝር በመዝገብ ከመያዝ ቸል ያለ እንደሆነ የልጁን ንብረት በውርስ ወይም በስጦታ ያገኘውን ሀብት በማናቸውም ሁኔታ ለማስረዳት ይቻላል።

፪. ሌላ ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር ምስክሮች በሚሰጡት ቃል አንድ ንብረት አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት እንደሆነ ይቆጠራል

አንቀጽ ፫፻፴ **1** <u>ሂሳቦችን ስለማጽደቅ</u>

፩. ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ የወጣው ልጅ የሞግዚቱን ሥራ ሂሳቦች ያጸደቀ እንደሆነና ዕድሜው ፲፰ ዓመት ያልሞላው ከሆነ ሂሳቦቹን ካጸደቀ በኋላ እስከ አንድ ዓመት ድረስ አጽድቆት የነበረውን ሂሳብ ራሱ ሊያፈርሰው ይችላል።

፪. ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ የወጣው ልጅ ሂሳብ እንዳያቀርብ ለሞግዚቱ ፈቃድ ሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ከዚህ በላይ ያለው ድንጋጌ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

፫. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ አካለ መጠን የደረሱ ሲወርሱት እነዚህ ወራሾች የልጁ ሞግዚት ያደረገውን ሂሳብ ያጸደቁት ወይም ሞግዚቱን ሂሳብ ከማቅረብ ነፃ አውጥተውት እንደሆነ ከዚህ በላይ ተመለከቱትን ድንጋጌዎች ጠቅሰው ለመከራከር አይችሉም።

አንቀጽ ፫፻፴ **2** <u>ስለ ይርጋ</u>

፩. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ወኪሎች ወይም ወራሾች በሞግዚትነት ሥራ ምክንያት በሞግዚቱ ላይ ስለኃላፊቱ የሚያቀርቧቸው ማናቸውም ክሶች ሞግዚቱ የሞግዚትነት ሥራውን ከተወበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት ሳያቀርቡ የቀሩ እንደሆነ በይርጋ ይታገዳል

፪. ሆኖም አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረቶቹ እንዲመለሱለት ለመጠየቅ ክስ የማቅረብ መብቱ ከዚህ በላይ የተመለከተው ጊዜ ካለፈ በኋላም ቢሆን አይከለክልም።

<u>ምዕራፍ አሥራ አራት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

አንቀጽ ፫፻፴ **3** <u>ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎችና ልማዶች</u>

ይህን አዋጅ የሚቃረኑ ሕጎች ደንቦች መመሪያዎች ውሳኔዎችና የአሰራር ልምዶች ይህን አዋጅ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም።

አንቀጽ ፫፻፴ **4** <u>በነባር ሕጎች መሰረት ተገኝተው ስለነበሩ መብቶች</u>

፩. ግልጽ የሆነ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት የነበሩ ሕጋዊ ሁኔታዎች ለማገኘት አዲሱ ህግ የሚጠይቃቸው መመዘኛዎች ከድሮው የተለዩ ቢሆኑም እንኳን በነባሩ ህግ መሰረት ተገኝተው የነበሩት ሕጋዊ ሁኔታዎች ሁሉ ፀንተው ይቀጥላሉ፣

፪. ግልጽ የሆነ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት በነበረው ህግ መሠረት ተገኝተው የነበሩት ሕጋዊ ሁኔታዎች ያገኟቸውን ውጤቶች ይህ ሕግ አይለውጣቸውም።

አንቀጽ ፫፻፴ **5** ስለምዝገባ

፩ የክልሉ መንግስት ይህ ሕግ በስራ ላይ በዋለ በአንድ ዓመት ውስጥ ምዝገባን ለሚሹ ጉዳዮች

የምዝገባ ሕግ ያወጣል፣ አስፈላጊ ተቋሞችንም ያደራጃል።

፪.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፭/ መሠረት የክብር መዝገብ ሹም ጽ/ቤት ተቋቁሞ ሥራን

እስኪጀምር ድረስ አግባብ ባለው አካል የተሰጠ ወይም የሚሰጡ የልደት፤የጋብቻና ሌሎች

አግባብነት ያላቸው የምስክር ወረቀቶች በክብር መዝገብ ሹም እንደተሰጡ ሰነዶች ተቆጥረው

ህጋዊነት ይኖራቸዋል።

አንቀጽ ፫፪፬ **6** ደንብ የማውጣት ስልጣን

1 የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ለዚህ ሕግ የአፈጻጸም ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

አንቀጽ ፫፪፬ <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ ከፀደቀበት ታህሳስ --- ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አርባ ምንጭ

ታህሳስ **-** ቀን **2016** ዓ.ም

ጥላሁን ከበደ

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር